# ሕይወቴ

# እና

# ጴንጠቆስጤአዊ እንቅስቃሴ

# አጀማመር

# በኢትዮጵያ

በመጋቢ ዘለቀ ዓለሙ (ዶ/ር)

©የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

አንደኛ ዕትም
ታኅሣሥ 2009 ዓ.ም

ኤዲተር፡- ወንድዬ ዓሊ(wondiyealihamza@gmail.com)
የሽፋን ንድፍ እና ገፅ ውበት በካሌብ በለጠ (kalebbelete42@gmail.com)

ለአስታየትዎ
በመጋቢ ዘለቀ ዓለሙ (ዶ/ር)
zelleke_alemu@yahoo.com

Printed in the USA
Signature Book Printing, www.sbpbooks.com

## ማውጫ

እመሰግናለሁ 8
መቅድም 10
መግቢያ 17
የአዲተሩ ማስታወሻ 21

ምዕራፍ አንድ 23
መነሻዬ 23
1. ዘለቀ - የባሊ አበዉ ልጅ 23
2. ሐረር መምሕራን ማሠልጠኛ 28
3. "አይበቃህም?!" 32
4. ገደብ በሌለው ጸጋ መወረስ 33
5. ያልተዘጋጀሁበት የጨለማ ኃይል ውጊያ 41

ምዕራፍ ሁለት 51
አስደናቂው ጰንጠቆስጤአዊ እንቅስቃሴ አጀማመር 51
6. ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ 'ፍንዳታ' 51
7. የመጀመሪያዋ የጰንጠቆስጠ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ አጀማመር 57
8. ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን 59
9. ጌታን የማገልገል ጥሪ 63
በናዝሬት የመንፈስ ቅዱስ መቀጣጠል 65
ሐረር (1957 ዓ.ም) 66
አዋሳ (ሐዋሳ) 1957 ዓ.ም 75
መስከረም 1959 ዓ.ም - አዲስ አበባ 80

ምዕራፍ ሦስት 81

የሙሉ ጊዜ አገልግሎትና የማልረሳቸው ትዝታዎቼ 81

10. ወደ ሙሉ ጊዜ አገልግሎት መሸጋገር 81

ባለ ጥምጣሙ ሰውዬ 89

ወንድም ሚካኤል ዳንኤል 91

ወንድም መርዕድ ለማ 95

ምዕራፍ አራት 101

የእንቅስቃሴው መስፋፋት 101

11. ጌታ በሚያስደንቅ ሁኔታ የጎበኛቸው ከተማዎች 101

ናዝሬት (አዳማ) 101

ወንጂ( ሸዋ) 104

ራሳ ጉባ 104

መቱ፣ ጎሬ፣ ጋምቤላ 108

ጎንደር 110

አዋሳ/ሐዋሳና እና አካባቢዋ 112

ምዕራፍ አምስት 121

ኢትዮጵያን ለቅቄ ወደ ስዊድን የመሄዴ ነገር 121

12. "ወሰጂ አስተምርሃለሁ" 121

ምዕራፍ ስድስት 131

አንደ ገና በምድሬ 131

13. የደስታና ሃዘን ጉራማይሌ 131

ምዕራፍ ሰባት 135

ሁለተኛው ዙር የመንፈስ ቅዱስ ጉብኝት በምድራችን 135

14. አገልግሎት ከወንድም ዳንኤል መኮንን ጋር 135

15. በጉብኝቱ መካከል - ትዳር 146

ምዕራፍ ስምንት 151

ቀሣም ባሕር ማዶ 151

16. ወደ ስዊድን 151

ተዓምራታዊ የጌታ አገዛ 154

17. የሚያስገርም ጥሪ 167

18. የመጀመሪያ ጉዞዬ ወደ አሜሪካ 169

ምዕራፍ ዘጠኝ 175

አገልግሎት በአሜሪካ ምድር 175

19. አስደንጋጭ ዜና (1984 እኤአ) 175

20. የዳላስ ቤተ ክርስቲያን አጀማመር 185

ሰንበት 195

21. ዴንቨር 200

በዴንቨር የአገልግሎት አጀማመር 201

22. አንደ ገና ወደ ዳላስ 209

ኤርትራውያን የሚያመልኩበትን ቤተ ክርስቲያን አጀማመር 211

23. የጸጥታ ዘመንና የመንፈሳዊ ሕይወት አመርታ 216

አዲስ የአገልግሎት ምዕራፍ 218

24. ሌላው አስገራሚ የአገልግሎት ጥሪ 224

ቨርጂኒያ አንደ ገና ከኤርትራውያንጋር 227

ምዕራፍ አስር 237
ያለፍኩባቸው አስፈሪ ልምምዶች 237
25.ከመከናወን በስተ ጀርባ 237
26.ግሩም ድል በጌታ 259
27.መደምደሚያ ነገር 266

እግዚአብሔር ለምድራችን ያለው የዘለዓለም ዕቅዱ 266
ልዩ የሆነው የምድራችን በመንፈስ ቅዱስ መጎብኘት 268



# አበርክቶት

ይህች መከራዬ:-

በመጀመሪያ ደረጃ:- ገና በለጋ ዕድሜሽ በከበረው የወንጌል አደራ መስከ ከእኔው እኩል ተጠምደሽ፣ ለተረዳሽው እውነት ወደ ኋላ ሳትይ በብዙ ስደትና መከራ የተጓዝሽበት ጎዳና ምን ያህል አስቸጋሪ እንደ ነበረ እረዳለሁ:::: በዚህ የከበረ ጥሪ እስከ እሁንም ድረስ አብረሽኝ ላለሽው፣ ለማከብርሽ ለውድ ባለቤቴ ወይንሸት እሰፋው (ፓ/ር) ማስታወሻ ትሁንልሽ።

እንዲሁም:- በረዥሙ የአገልግሎት ዘመናችን እኔና ወይኒ ባሳለፍናቸው የማጣትና የማግኘት፤ የስደትና የመከራ ጊዚያት ሁሉ፣ ልናደርግላችሁ ሲገባን ነገር ግን ያጎደልንባችሁ ብዙ ነገሮች እያሉ፣ ገድላታችንን ከምንም ሳትቆጥሩት በፍቅር አብራችሁን ለተጓዛችሁ ልጆቻችን ለወንጌል ዘለቀ፣ በአገልግሎት ከባለቤትሽ ጋር ለተጠምድሽው ለዲቦራ ዘለቀና የጌታ ቆራጥ ወታደር ለሆንከው ለሳሙኤል ዘለቀ ማስታወሻ ይሁን።

በተጨማሪም እሁን ይህንን የወንጌል ችቦ ይዘው ለሚሮጡ ጌታ እንደ ተናገረው ቃል በምድራችን ላስነሳው አዲስ ትውልድና ለአብያተ ቤተ ክርስቲያናት ሁሉ ትሁንልኝ።

# አመሰግናለሁ

ከሁሉ አስቀድሜ በመጀመሪያ ለወደደኝ ከኃጢአቴም በደሙ ላጠበኝ ለአባቱም ከካኅናት መንግሥታት መካከል እንድሆን ላበቃኝ፣ አዳኜና ጌታዬ ለሆነው፣ በክብርና በምስጋና ለተሞላ፣ ጸጋውና ምህረቱ ለተትረፈረፈ፣ ግሩምና ድንቅ ለሆነው እየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ክብርና ምስጋና ከዘለዓለም እስከዘለዓለም ይሁንለት፡፡

እሱ ነው! «ከቶም አልተውህም፣ አልጥልህም፤» ብሎ ገና በእንጭጭ የክርስትና ጉዞ ጅማሬዬ ላይ ተስፋን የሰጠኝ፤ ታማኝነቱን ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ሳያጓድል፣ ስወድቅ እያነሳ፣ ስፍገመገም እየደገፈ፣ ተስፋ ሰቆርጥ ተስፋዬን እያደሰ፣ ከፈቃዱ ስወጣ ወደ ፈቃዱ እየመለሰ፣ በሐሩሩና በምድረ በዳውና በረግረጉ እስፈሪ ጉዞ ላይ በከንዱ ደግፎ ከአምላ አመታት በላይ በቤቱ ያቆየኝ፡፡

አገልግሎቴ በአብዛኛው እብያተ ክርስቲያናትን መትከል ነውና በዚህ በሁሉም እቅጣጫ እጅግ ዋጋን በሚያስከፍል አገልግሎት ከጎኔ በመቆም፣ ከእኔው እኩል አብራኝ ዋጋን በመክፈል ድጋፏ ሳይለየኝ፣ እስከ ዛሬም ድረስ ከእህጉር ወደ እህጉር፣ ከአገር ወደ እገር፣ ከስቴት ወደ ስቴት ለተንከራተተች፣ ባለቤቴ ወይንሸት ዓለሙ እግዚአብሔር እብዝቶ አብዝቶ ይባርከሽ እላለሁ። የእሷ ማነሳሳትና ማበረታት ባይታከልበት ይህ መጽሐፍ ለኅትመት ባልበቃ ነበር፡፡

ይህን ታሪክ ወደ መጽሐፍነት እንድ ለውጠው ከገፋፉኝ ሰዎች መካከል የዚያን ዘመን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በተለያዩ ሥፍራዎች በምስከርነት ስናገር የሰሙ ወገኖቼ ናቸው፡፡ የሁሉንም ስም ዘርዝሬ እልችለውምና ምስጋናዬ ለሁላችሁም ይድረስ እላለሁ።

ወደ መስናዶውና የኅትመቱ ጉዳዮች ልመለስና፡- ይህ መጽሐፍ ለኅትመት የበቃው ጌታ እግዚአብሔር ምህረት አለግድን ከጀርባዬ ስለ አቆመልኝ ነው፡፡ ወይዘሪት





ምህረት፡- የዚህ መጽሐፍ ኤዲተር የሆነውን ወንድዬ ዓሊን በማፈላለግ፣ በእጅ ጽሑፈት የላኩላትን ረቂቅ በማስተየብ፣ የተተየበውን አርማ እንደገናም እንደገናም ሳትሰለች በማጻፍ አገዘችኝ፡፡ ምህረት ጌታ እብዝቶ ይባርከሽ!

መጽሐፉን ያቀነባበረልኝ ወንድዬ ዓሊ ነው፡፡ ፊት ለፊት ሳይሆን በሦስተኛ ወገን በኩል እየተመካከሩ መጽሐፍ ማዘጋጀት የተለመደ ነገር አይመስለኝም፤ ወንድዬን በጣም ላመሰግነው እወዳለሁ።

ረቂቁን አንብቦ ግሩም መቅድም እንዲጽፍልኝ የጋበዝኩት መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳን የጠቆማቸው ቁልፍ ነጥቦች መለኪያ የላቸውም፤ ስለ ሃሳብ ልግሥናህ አመሰግንሃለሁ - ወንድሜ፡፡

በተጨማሪ አገልግሎቴን እጅግ ፈታኝና አስቸጋሪ ባደረጉብኝ ወቅት ከእኔ ሳትለዩ አብራችሁኝ በጸሎት በምክር የደገፋችሁኝን፣ ወንድሞቼ ሐዋርያው ዳንኤል መኰንን፣ ፓስተር ቶሎሳ ጉዲና(ዶ/ር)፣ እንዲሁም ሌሎቻችሁን በዚህ መጽሐፍ ላይ ስማችሁን መጻፍ ያልቻልኩትን ጌታ እትረፍርፎ ይባርካችሁ እላለሁ።

# መቅድም

«ማን ያውራ? የነበረ ...» እንዲሉ፥ የኢትዮጵያን ጴንጤቆስጤአዊ እንቅስቃሴ አጀማመር መተረክ ከሚችሉት ጥቂት ሰዎች መካከል አንዱ መጋቢ ዶክተር ዘለቀ ዓለሙ ነው። ምክንያቱም እርሱ በጊዜው፥ በቦታው፥ በውስጡ፥ ነበረ። እርሱ ለዚያ ታሪክ «የዓይን ምስክር» ብቻ ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር በታች፥ ዋና ተዋናይም ጭምር ነበረ። በዚያ ታሪክ ዙሪያ ለሚያጠነጥነው ለዚህ መጽሐፍ መቅድም እንድጽፍ በመጠየቄ ራሴን እድለኛ እንደ ታደለ ሰው እቆጥረዋለሁ።

በመቅድሜ፥ በዚያ ጅማሬ ውስጥ ያስተዋልኳቸውንና ትኩረቴን የሳቡትን ስምንት ነጥቦች በጫጭሩ ላነሣ እፈልጋለሁ። እንደዚህ የማደርገው ከእነዚህ ነጥቦች አብዛኞቹ ቀጣይነት ስለሚኖራቸው፥ እንድናውቃቸውና በሚከሰቱ ጊዜም እንድናስተናግዳቸው ለማሳሰብ ያህል ነው።

ሀ) ጊዜ፡- እግዚአብሔር ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ዝርዝር መርሐ ግብር አለው፣ ብዬ አምናለሁ። በዝርዝሩም ውስጥ አንዱና ወሳኙ ነገር ጊዜ ነው። በኢትዮጵያ በሃያኛው ክፍለ ዘመን፥ በቁጥር ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች ላይ፥ ለመጀመሪያ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ «የፈሰሰው»፥ በ1954 ዓ.ም. ክረምት፥ በሐዋሳ የስዊድን ፊላደልፍያ ሚስዮን፥ የልጆች የጸሎት ፕሮግራም ላይ ነው። እሱ ከሥተት እዚህ መጽሐፍ ውስጥ አልተጠቀሰም።

አንደኛው የዚህ «አጀማመር» አካል ስለ ሆነ፥ በዚህ መቅድሜ ውስጥ እኔ አካትቼዋለሁ። በጸሎት ፕሮግራሙ ላይ የነበሩት «ልጆች» አምስት ብቻ ይመስሉኛል። በድንገት፥ በሁሉም ላይ መንፈስ ቅዱስ ፈሰሰባቸው። የጸለየላቸው ወይም እጁን የጫነላቸው ሰው አልነበረም። መሬት ላይ ወድቀው እየተንከባለሉ በልሳኖች ተናገሩ። አንድ ኢትዮጵያዊ ልጅ በስዊድንኛ፥ የአሥራ አንድ ዓመቷ ክሪስቲና ራምስትራንድም (የሚስዮኑ ኃላፊ ልጅ) በኢንግሊዝኛ ቋንቋዎች ትንቢት ተናገሩ። ኢትዮጵያዊው ልጅ ስዊድንኛ፥ ክርስቲናም ኢንግሊዝኛ አይችሉም ነበር። ሚስዮናውያኑ ተደናገጡ።[1]

ሁለተኛውም «መፍሰስ» የሆነው በዚያው በሐዋሳ በነሐሴ ወር 1955 ዓ.ም. ኬንያዊው ቻቻ ኦማሄ ባገለገለበት ኮንፈረንስ ላይነው።

ሦስተኛው «መፍሰስ» የሆነው ከሐዋሳው ኮንፈረንስ መልስ፥ በመስከረም ወር 1956 ዓ.ም.፥ ቻቻ ኦማሄ አዲስ አበባ መርካቶ በሚገኘው የፊንላንድ ሚስዮን ባገለገለ ጊዜ ነው።

አራተኛው - ከኅዳር ወር 1956 ዓ.ም. ጀምሮ፥ በሐረር መምህራን ማሰልጠኛ ተማሪዎች መካከል የፈሰሰው ሲሆን፥

አምስተኛው - በ1957 ዓ.ም. በናዝሬት የሰማይ ብርሃን ወጣቶች (የዓፄ ገላውዴዎስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች) መካከል የፈሰሰው ነው።

ስድስተኛው - በ1958 ዓ.ም አዲስ አበባ አራት ኪሎ፥ «አራቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች» በተከራዩት ቤት ውስጥ የተከሠተው ፍንዳታ ነው። ከዚያ በኋላ የሆነውን ሁሉ እየተከታተሉ አንድ ባንድ መዘገብ- ባጭሩ - የሚቻል አይመስለኝም። ጌታ ግን ያንን ጊዜ የመረጠው ለምን ይሆን?

ለ) ዕድሜ፡- ከላይ እንዳየነው፥ እንቅስቃሴው የጀመረው በታናናሽ ልጆች ነው። ከዚያም ባመቱ ወደ ወጣቶች ዘለለ። ለምሳሌ ዘለቀ መንፈስ ቅዱስ ሲወርድበት የ16ዓመት፥ የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌና ቀጥሎም ወንጌላዊዋ ሲሆን የ19 ዓመት እንዲሁም የሐዋሳ ፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ዋና መጋቢ ሲሆን ደግሞ የ22 ዓመት ወጣት ነበር። ይገርማል! ጌታ ግን ያንን ዕድሜ የፈለገው ለምን ይሆን?

ሐ) ዳርቻ፡- የዚያ እንቅስቃሴ መከሠቻ ኢትዮጵያ (ኤርትራን ታካትታለች) ብትሆንም፥ ዳርቻው ግን መላው ዓለም ነው። ይህንን በሚመለከት ከእንቅስቃሴው ጅማሬ ጀምሮ ትንቢቶች ይነገሩ እንደ ነበረ ዘለቀ ያስታውሳል።

እርሱ እንደሚለው፥ ያ እንቅስቃሴ እንዲያውም በዓለም ዙሪያ ከተከሠቱ እንቅስቃሴዎች በተለየ ሁኔታ፥ እስከ ዛሬም ድረስ ያልበረደ፥ ይልቁንም ከኢትዮጵያውያን አልፎ ወደ ሌሎች ሕዝቦች ሲዘልቅ መንደርደር የጀመረ፥ ታላቅ እንቅስቃሴ ነው። በእንቅስቃሴው የመጀመሪያ ቀን እነዚያ «ሁለት ልጆች» የተነበዩት ስለዚሁ ጉዳይ ይሆን?

መ) መስሕብ፡- እንቅስቃሴዎች ሁሉ የየራሳቸው መስሕብ አላቸው። የጴንጤቆስጤአዊው እንቅስቃሴ መስሕብ፡-የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፥ እርሱንም የሚከተሉት በአዲስ ቋንቋ መናገር፥ ተአምራት፥ ምልክቶችና ድንቆችናቸው። ጌታቸው ምክረ እንዴት እንደ መሰከረለት ሲጽፍ፥ ዘለቀ እንዲህ ይላል፡- «አንድ ቀን ለብዙ ወራት በውስጤ ሊቀር የቻለ ነገር ተናገረ። እዚያ እርሱ ይከታተል በነበረው ፊኒሽ ሚሽን የቤተ ክርስቲያን መጋቢ የነበሩት ሴት ሚሰዮናዊ «ዛሬም እንደ ሐዋርያት ዘመን መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ ሲናገሩ ሰምቻለሁ» አለኝ። ይህን ጊዜ እሳቤ ሁሉ ወደ ተናገረው ነገር ተሳበ።»

በሌላ ጊዜ የሆነውን ደግሞ እንዲህ ይተርከዋል፡- «ምነው መንፈስ ቅዱስ የወረደበትን ሰው ሳታመጣልኝ» አለው - አስተማሪውን ወጣት። «አስተማሪውም ወደ እኔ በጣቱ እያመለከተ፡- እሱ እኮ ነው!» አለው። በዚህ ጊዜ እኔ እየሰማሁት፡- «እንዴ! ይኸ ዱርዬው! ... እንዴት መንፈስ ቅዱስ ወረደበት?» አለ። ይህንን ንግግር የተለዋወጡት አስተማሪው አሰፋ ዓለሙና ለሞት በሚያደርስ የደም ካንሰር ታምሞ የነበረው ቤተ መንግሥቱ ናቸው።

ሠ) የጀርባ አጥንት፡- የእንቅስቃሴው መስሕብ ልምምዶቹ ቢሆኑም፥ የጀርባ አጥንቱ ግን ቃለ እግዚአብሔር ነበረ። በአርባዎቹ መጨረሻ እና በኀምሳዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ሁለት ጴንጤቆስጤአውያን የሚሰዮን ድርጅቶች ነበሩ። ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በጊዜው እንግዳ የነበረውን አስተምህሮ መዝራት የጀመሩት እነርሱ ናቸው። ኬንያዊውን





ቻቻን ያስመጣው የሐዋሳው የስዊድን ፊላደልፍያ ሚሰዮን ቢሆንም፥ የመርካቶው ፊንላንድ ሚሰዮንም ወጣቶቹን እንዲያገለግልላቸው ጋብዞታል። ሁለቱም ሚሰዮኖች የቻቻን አገልግሎት የፈለጉት ጴንጤቆስጤአዊውን አስተምህሮ ከጴንጤቆስጤአዊው ልምምድ ጋር እንዲያስታርቅላቸው ነበር። በዚህ ሂደት ውስጥ ሁለቱ የሚሰዮን ድርጅቶች ተልዕኳቸውን ተወጥተዋል። በተለይም የስዊድን ፊላደልፊያ ሚሰዮን ከመላ አገሪቱ ወጣቶችን በራሱ ወጭ በየዓመቱ በሐዋሳ እየሰበሰበ ለሦስት ሳምንታት በቃለ እግዚአብሔር ያስታጥቃቸው ነበር።

ረ) አመራር፡- መንፈሳዊነትና ነፍሳዊነት በጣም የሚመሳሰሉ፥ ነገር ግን በጣም የተራራቁ ነገሮች ናቸው። እነዚህ ሁለቱ አንዳንድ ጊዜ ለመለየት እንኳን ያስቸግራሉ። በጴንጤቆስጤአዊው እንቅስቃሴ ውስጥ ትልቁ ተግዳሮት (challenge) በአንድ በኩል መንፈስ ቅዱስ እንዳይከለከል፥ በሌላ በኩል ደግሞ ነፍሳዊነት እንዳይሰለጥን ጥንቃቄ ማድረግ ነው። እንደዚህ ካሉት ተግዳሮቶች ውስጥ ዘለቀ ስለ አንዱ እንዲህ ይላል፡-

> «በኅዳር 1957 ዓ.ም. ወንድም አሰፋና እህት ሙሉ ቤታቸው የጸሎት ቤት እንዲሆን ከፈቱልን ... እኔም አንዳንድ ያልተውኳቸው፥ አሁን ሳስበው የሚያስቁኝ፥ ዓመቱን ሙሉ የምለማመዳቸው ልምምዶች ነበሩኝ። መንፈስ ቅዱስ ስሞላ፥ የእግዚአብሔር ኃይል ሲወርድብኝ ወድቄ ነበር። አሁንም ያንን ልምምድ አልተውኩትም ነበር። የእግዚአብሔር ኃይል ሲመጣ በልሳን እጸልይና የሚጥለኝ ነገር ባይኖርም ... እወድቅ ነበር። ታዲያ እነ እሴ ቤትም ተሰብስበን ስንጸልይ ... እኔ ስወድቅ እነሱም (አሰፋ እና ቤተ) በዚያ ቁመታቸው ይወድቁ ነበር ... ከበደ ወ/ማርያም ከአዲስ አበባ መጥቶ፥ 'እንደዚህ ማድረግ እኮ አስፈላጊ አይደለም፤ ዝም ብላችሁ በመንፈስ ቅዱስ እየጸለያችሁ፥ ሳትወድቁ ጸጋውን መለማመድ ትችላላችሁ' ብሎ ካስተማረን በኋላ የመውደቁ ነገር እዚያ ላይ አበቃ።»

ሸ) ትስስር፡- ይህ መጽሐፍ የሚተርከው ስለዚያ እንቅስቃሴ አጀማመር ነው። ቦታዎቹ አምስት፥ ከሥተቶቹ - እኔ አንድ ጨምሬባቸው- ስድስትቢ ደርሱም እንኳን፥ በመካከላቸው ግን ብርቱ ትስስር ነበረ። ይህንን ብርቱ ትስስር ለማሳየት ከአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት የተሻለ ማስረጃ አይገኝም። በ1959 ዓ.ም. ከተሾሙት ከመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሰባት ሽማግሌዎች ውስጥ ሦስቱ ከመርካቶው ፊንላንድ ሚስዮን፥ ሦስቱ ከሐረር መምሕራን ማሰልጠኛ ተቋም፥ አንዱ ከሀዋሳ የስዊድን ፊላደልፍያ ሚስዮን የመጡ ነበሩ።

ቀ) የቤተክርስቲያን ተሐድሶና ተከላ፡- ያ እንቅስቃሴ ተጓዥ ነበረ። በየደረሰበት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ክርስቶስ ይሰበካል፤ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃሉ፤ ነባር አብያተ ክርስቲያናት ይታደሳሉ፤ አዳዲሶችም ይተከላሉ። የሪቫይቫሉ ፍሬ «አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት» በሚባሉ ጎተራዎች ውስጥ ይከተታል። ዛሬ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት - በሙሉ ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ - «ካሪዝማዊ» የሆኑት፥ የምዕመናኑም ቁጥር እንደዚህ የተመነደገው፥ ከዚያ እንቅስቃሴ የተነሣ ነው ብንል ማጋነን አይሆንም። ተሐድሰው ለወንጌል አገልግሎት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ወደ ነበሩ ሚስዮናውያን፥ በእነርሱም አማካይነት በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ወዳሉ ወደ ሌሎችም ጭምር ተጉዟል። ዘለቀ በመጽሐፉ ውስጥ ከጠቀሳቸው ሁለቱን ብቻ እንሥቼ መቅድሜን ልቋጭ።

የመጀመሪያው፡-

«አሰፋ ዓለሙ፥ ቤተ መንግሥቱና እኔ አዲስ አበባ በሚገኘው፥ የፕሪስቢቴርያን ሚሽን በነበረው፥ የአሜሪካን ሚሽን ትምሕርት ቤት በምናስተምርበት ወቅት ብዙዎቹ ሚስዮናውያን በተሞላነው የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ለጌታ አገልግሎት ባለን ጥማት በጣም ይደነቁ ነበር ... በ1960 ዓ.ም. በሰኔ ወር እኔንና ቤተን ሙቱ ሄደን እንድናገለግል ጠየቁን ... በጊዜው ባናውቀውም፥ ለካ ሚስዮናውያኑ የወንጌል ፍሬ ስላላዩበት ከ50 ዓመታት የድካም ዘመን በኋላ የወንጌል ጣቢያቸውን ለመዝጋት የቆረጡበት ጊዜ ነበር ... እኛ ከጎሬ ከተመለስን ... በኋላ ዶ/ር ከሳርከ አዲስ አበባ ወንድም አሰፋ ዓለሙ ቤት መጥቶ ሳለ፥ ጌታ በጣም በሚያስደንቅ ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ ሞላው። ከዚያም ዶ/ር ሚለር ከባለቤቱ ጋር የምናድርበት ጸሎት ቤት ድረስ መጥተው እኔና ወንድም አሰፋ ዓለሙ ጸለይንላቸው። ጌታም በሚያስደንቅ ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ ሞላቸው ... የአሜሪካን ሚሽን ትምሕርት ቤት ዳይሬክተር የነበረችው ሚስ እንደርሰን የተባለችውም በመንፈስ ቅዱስ ተሞላች ... በመጨረሻም ሚስዮናውያኑ እንዳሰቡት ሳይሆን፥ ጣቢያቸውንም ሳይዘጉ፥ ይልቁንም እነርሱንም መንፈስ ቅዱስ ጎብኝቷቸው፥ በጎሬም የተቀጣጠለው የመንፈስ ቅዱስ እሳት ከፍለ ሀገሩን አዳርሶ ... ።»

ሁለተኛው -እንደ እ.ኤ. በ2008 ዘለቀ በላንካስተር (አሜሪካ) በተካሄደ የሜኖናይቶች ስብሰባ ወቅት የሰማው ነው፡-

«ስብሰባው ... ዱሮ ኢትዮጵያ ሳለን የምናውቃቸው ሚስዮናውያን እጆቻቸውን ወደ ላይ ዘርግተው ጌታን ሲያመልኩ በልሳንም ሲናገሩ ያየንበትና የሰማንበት ነበር። ይሄ ደግሞ የቀድሞ አቋማቸውን ለሚያውቅ እጅግ አስደናቂ ተአምር ነው ... እናም የዚህን ታላቅ ለውጥ መንስዔ ለማወቅ እጅግ ጓጓሁ ... ሜኖናይቶችን ምን ነካቸው? እንዴት በዚህ ዲኖሚኔሽን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ሊገባ ቻለ? ብዬ ጠየቅኋቸው ... እርሳቸውም (ናታን ሄጊ) ለሚሽነሪ አገልግሎት ኢትዮጵያ በነበርንበት ጊዜ ነበር ሰሎሞን ከበደን የተዋወቅነው። እርሱ ነበር ወደዚህ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ውስጥ ያስገባን። እርሱ ደግሞ ይህንን ... ልምምድ ጌታ ባንተ በኩል ወደርሱ እንዳመጣው ነግሮኛል፤ እኔም በጻፍኩት መጽሐፌ

ውስጥ እስፍሬዋለሁ አሉኝ ... በምድራችን ከአንዲት ደሳሳ የጸሎት ቤት (የሰማይ ብርሃን) የወጣው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ... ባሕር ተሻግሮ፥ በአሜሪካ ምድር አዲስና በጽድቅ የተመሠረተ ድርጅት እንዲቋቋምም ያደረገ ነበር ... ኢትዮጵያን ለአሜሪካ የቀረሰ፥ በረከት ያደረጋት ያ የመንፈስ ቅዱስ እሳት ዛሬም ሕያው ነው፤ ገና ለዓለም ሁሉ መድኀኒት ያደርጋታል።» አሜን! ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሁን።

በቀስ ወልደ ኪዳን (መጋቢ)





## መግቢያ

ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ያስቆጠረ የመንፈስ ቅዱስ መንብኘት ምድራችንን እየቀሰቀሰ አልፎም ተርፎም በዓለም ዙሪያም ተፅዕኖ እያመጣ ይገኛል ። አጀማመሩ ከአእምሮ በላይ እጅግ አስደናቂ ነበር፡፡ የዓይን ምስክር የሆንንም አገልጋዮች አስን፡፡ እግዚአብሔር እድሜ ጨምሮልን ዛሬ ላይ የደረስን ወገኖች ያን አስደናቂ የመንፈስ ቅዱስ መንብኘት ሰቀሪው ትውልድ የማስተላሰፍ ኃላፊነት አንዳስብን አረዳሰሁ፡፡ የአቅማችንን ካቀበልን፣ ተቀባዩ ትውልድ የበሰጠ በጥናትና ምርምር ታግዞ ሙሉ ታሪኩን ስመተንተን መነሻ ይሆነዋልና።

የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ዓላማ በአራት ቁልፍ ነጥቦች መመደብ ይቻላል፡-

- በመጀመሪያ ብዙዎቻችን ባናውቀውም ይህ የዘለዓለም አምላክ እግዚአብሄር ኢትዮጵያ ተብላ ለተጠራችው ምድራችን እስከ ዛሬም ያልተለወጠ የዘለዓለም ዕቅድና ሃሳብ እንዳለው መግለጽ፤
- ከሃምሳ ዓመታት በፊት ጌታ በምድራችን ላይ የጀመረውን ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴና፣ ዘለዓለማዊ ፈቃዱን የገለጸበትን አሠራር ላለውና ለሚመጣው ትውልድ ማሳየት፤
- ለእንቅስቃሴው መለኮስና መስፋፋት በግምባር ቀደምነት እግዚአብሔር መሣሪያው አድርጎ የተጠቀመባቸውን ግለሰቦችና ሕብረቶች አስተዋፅዖ ማስታወስ (መዘከር)፤ እንዲሁም፡-
- በእነዚህ ጀማሪ ግለሰቦች አማካኝነት የመንፈስ ቅዱስ እሳት በመጀመሪያ ደረጃ ስለ ተበተነባቸው የኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞችና ከፍለ ሐገራትና ስለ መጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ጰንጠቆስጣዊት ቤተ ክርስቲያን የአመሠራረት ሂደት ማመልከት፤

መቼም በዓይን ምስክርነትና በግል የሕይወት ልምምድ (ተሞክሮ) ላይ ተመስርቶ መጽሐፍ ሲዘጋጅ የአንደኛ ደረጃ ነጠላ መደብ አተራረክ መከተሉ የታወቀ ነው ።

ስለሆነም ‹እኔ-እኔ› የሚለው ቃል በየመስመራቱ ተደጋግሞ መከሰቱ አይቀርም ። ለብዙዎች ታሪክ ሠሪ የሆነውን የጌታን ክብር የሚሻማ ቢመስል አይገርምም ። እኔ በግሌ አማራጭ እጦቼ ነው እንጂ ባሰፉት ሃምሳ ዓመታት እግዚአብሔር በምድራችን የሠራውን ጌታ በታላቅ አክብሮት እየመሰከርኩ ሳለሁ ‹እኔ› የሚለውን ቃል ሳስገባ የሆነ የውስጥ ህመም ይሰማኛል:: ሆኖም ጌታ በምድር ላይ ሲሠራ የሰዎች ልጆችን በተሰይ ደካማ የሆኑትን በመጠቀም ነውና ‹እኔ› ስል በፍጹም ትህትና ውስጥ ሆኜ መሆኑን አንባቢያን እንዲገነዘቡልኝ አደራ እላለሁ::

እውነተኛው ወንጌል ሐዋሪያት የሰበኩት የዛሬ ሁለት ሺ ዓመት ከእየሩሳሌም ወጥቶ ወደ ሰማሪያ ከደረሰ በኋላ ወደ እውሮፓም ሳይገባ፤ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በፊሊጶስ አማካኝነት ወደ ምድራችን እንዲገባ መደረጉ የአጋጣሚ ነገር ሳይሆን ሁሉን እንደ ራሱ ፈቃድ የሚሠራ የዘለዓለም አምላክ ስላቀደውና ስለወሰነው ነው።

በቀደምትነት ምድራችን የተቀበለችውን፣ የልተሸቃቀጠውንና ያልተበረዘውን፣ ሐዋርያት የሰበኩትን ወንጌል ብትኖርበትና ብታስተምረው ኖሮ፣ ለራሷም ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ሁሉ የወንጌል ፋና ቀዳጅ የደኅንነት በረከት አምጭም በሆነች ነበር:: ዛሬ ግብጽ፣ ሱዳን የአፍሪካ ቀንድ ተብሎ የሚጠራው ሁሉ በእስልምና ኃይማኖት ተጽዕኖ ውስጥ እይወድቁም ነበር:: ለኬኒያ፣ ለዩጋንዳ፣ ለታንዛኒያ፣ ለሌሎችም አፍሪካ አገራት የአውሮፓ ሚስዮናውያኖች ባላስፈለጋቸውም ነበር።

ሆኖም በታሪክ እንደተመለከትነው በዚህ በእግዚአብሔር እቅድና ሃሳብ ውስጥ ስላልቆየች፣ በቀደምትነት የተቀበለችውንም ንጹህ ወንጌል በባእዳን ልምምዶችና አምልኮ ስለ በረዘችው ተደጋጋሚ የእግዚአብሔርን ግሣጼና ቅጣት የቀመሰች አገር ሆነች::

በተለይ ይህን የእውነት ወንጌል ተቀብለው ያገለገሉትንና ተሃድሶ ለማምጣት የሞከሩ መነኮሳትንና ካህናትን ቀሳውስትን ምእመናኑንም ጭምር ቋንጃና ምላስ





በመቁረጥ፣ እፍንጫ በመፎነን፣ የቀሩትንም ከአንገት በታች በመቅበር የቀንድና የጉማ ከብት በራሳቸው ላይ በመንዳት ሰወንጌል ታላቅ ሰማዕትነትን በእነ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የተፈጸመው ግፍ ቀላል አልነበረም። ከዚያ በኋላ ለአምስት መቶ ዓመታት በታሪክ የተደገፈ የተሃድሶ ዘመን በምድራችን አልታየም:: የዝምታና የጸጥታ ዘመን ሆኖ አለፈ::

ኢትዮጵያን የማይረሳ ጌታ ከአምስት መቶ የጸጥታ ዓመታት በኋላ እንደ ገና ማስትም በእስራ ዘጠኝ ሃምሳዎቹ አጋማሽ ላይ ጌታ የመታደስን ዘመን እንደገና ወደ ምድራችን አመጣ:: ልክ እንደ ሐዋርያት ዘመን መንፈስ ቅዱሱን በማፍሰስ አዲስ ጉብኝቱን ጀመረ። በዚህ ጊዜ ግን መጎብኘቱ የጀመረው ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ነበር። ባለፉት ሃምሳ ዓመታት በምድራችን የተቀጣጠሰው የመንፈስ ቅዱስ እሳት በይዘቱም ሆነ በእሠራሩ በሌሎች አገሮች ላይ እንደተከሰተው ዓይነት ሳይሆን የተለየ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

በታሪክ እንዳነበብነው አንድ የመንፈስ ቅዱስ መጎብኘት በአንድ አገር ላይ ከአርባ አመታት በላይ አይቆይም፤ በአንድ ወይ በሌላ ነገር ይከስማል፣ ይጠፋል፤ ወይንም የራሱን ቤተ ሃይማኖት መስርቶ ኃይሉንና እሳቱን አጥቶ ይቀጥላል። የምድራችንን መጎብኘት ልዩ የሚያደርገው ከሃምሳ ዓመታት በሁዋላ መቀጠሉና ሁሉንም በምድራችን ላይ ያሉት ቤተ ሃይማኖቶች ውስጥ ገብቶ ተሃድሶን ማምጣቱ ነው ። በዓለማችን ላይ እንደዚህ ያለ መጎብኘትን ያገኙ የዲኖሚኔሽኖችን ግድግዳ መንፈስ ቅዱስ አፍርሶ ተሃድሶን ያገኙ እንዳሉ እኔ አላውቅም:: ይህ ነው በይዘቱም ሆነ በአሰራሩ በምድር ላይ ከተከሰቱት የመንፈስ ቅዱስ መጎብኘቶች የኢትዮጵያን ጉዳይ ልዩ የሚያደርገው።

ይህንን በአገራችን ታሪክ ልዩ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ መጎብኘት የዓይን ምስክር ያደረገኝን፣ ምስክርነቴንም በመጽሐፍ መልክ እንዳዘጋጅ የረዳኝን አምላኬን እየመሰገንሁ ሙከራዬን እነሆ ብያለሁ::

አንባቢያንም ካለፈው ታሪክ በመማር በመጨረሻው ዘመን ወደ ምድራችን በሙላት ሊመጣ ስላለው መነቃቃት «የእኔስ ድርሻ ምንድን ይሆን? በማለት የጌታን ፈቃድና ምሪት ዘወትር እንድትጠይቁ በጌታ ፍቅር አሳስባለሁ።

መልካም ምንባብ





# የኤዲተሩ ማስታወሻ

ዕድሉ ፈንታዬ ሆኖ የሥነ ጽሑፍ ወዝ አደር ከሆንኩ ሰነበትኩ፣ በሙያዬ እንዳገለግላቸው ከጠሩኝ ሰዎች መካከል አንዱ መጋቢ ዶ/ር ዘለቀ ዓለሙ ሆኑ ፡፡ ገና በገጥ ሳንገናኝ የመጽሐፉቸው መሰናዶ አለቀ፡፡ ትልቁን የኃላፊነት ሸክም የተወጣችው መካከላችን ወይዘሪት ምህረት አሰግድ ነበረች፤ ልባም ልጅ፡፡

ከደራሲው ወይንም ከመጽሐፉ ባለቤት ጋር ፊት ለፊት ሳልገናኛ የአርትዖት ሥራ ሳከናውን የጀመሪያዬ ነው፡፡ ለማንኛውም ይህን ጨዋ ምስክርነት ወደ ኅትመት እንዲደርስ እግዛቸው ዘንድ ስለጠሩኝ ዶ/ር ዘለቀ ዓለሙን አመሰግናለሁ፡፡

ዶ/ር ዘለቀ ዓለሙ፡- የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ በጥቂትት የጽሞና ቁጭታ ነበር የጻፉት፡፡ የመጀመሪያዎቹን ሰባ ገጾች አስታውሳለሁ፤ ሽሮ ቀለም ባለው ሉክ ነበር በእጅ ጽሑፍ የላኩት፡፡ ተከታታዮቹን ግርድፍ ረቂቆች ምህረት አሰግድ ተረክባ ለተያቦች ታቀብል ነበር፡፡ መጀመሪያ ወይዘሪት ብርሃን ጉና ቀጥሎም ወይዘሮ ሠቢት ኑራሞ ተየቡት፡፡ በተቻላት መጠን አቧራውን ያራገፈችልኝ ወይዘሮ እልሳቤጥ ሃሰን ነች፡፡ የኖኄያት እና የትምህርተ ጥቅስ ወጥነት መጣረሳቸው እንደ ተጠበቀ - ሁላቸው ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

መጋቢ ዶ/ር ዘለቀ ዓለሙ፡- የመጀመሪያና ሁለተኛ ድግሪያቸውን ያገኙት ከሥጣኔ ሐብት ጋር በተያያዙ ትምህርቶች ነው፡፡ ሌላ ሁለተኛ ማስተርሳቸውንና ሦስተኛውን ድግሪያቸው የሠሩት ደግሞ በሥነ መለኮት ዘርፍ ነው፡፡ መጽሐፉቸው ግን በድግሪዎቻቸው መጠን የተኮሸ አይደለም፡፡

ያልቁንም እግዚአብሔር በእሳቸውና በዘመን እቻዎቻቸው የፈጸመውን ጴንጠቆስጤው እንቅስቃሴ በመደበኛ የመድረክ ምስክርነት መልክ ለማቅረብ ወደዱ፡፡ ከሃምሳ ዓመት በፊት ስለ ነበረው አዲስ መንፈሳዊ ክስተት ከመተረክ በተቀር ሥነ መለኮታዊ ትንተና ለመስጠት አለመሞከራቸው በተመሳሳይ መንገድ

ከአገዝኳቸው ሰዎች መጽሐፋቸውን ልዩ ያደርገዋል፤ ደስ አሰኘኝም።

በእርግጥ፡- ሃምሳ ዓመት ያህል የፈጀውን ታሪክ ከትዝታ ማህደራቸው ጎርጉረው በገርነት ሲያቀብሉን፣ የእያንዳንዱን መንፈሳዊ ክስተት፣ በቀንና በዓመት፣ በጊዜና በሥፍራ፣ የታሪኩ ተዋንያን ድርሻ መጠን፣ እንዲሁም ስምና በቅደም ተከተል ረገድ ፍጹም ይሆን ዘንድ መጠበቅ ሌላ ገርነት ይጠይቃል።

ይሁን እንጂ ይህ መጽሐፍ ከግማሽ ከፍለ ዘመን በፊት ለመንግሥትም፣ ለአብያተ ክርስቲያናትም ለማሕበረሰባትም፣ ወዘተ እንግዳ ነገር የነበረውን ጰንጠቆስጢአዊ እንቅስቀሴ አጀማመርና መስፋፋት ለመመስከር ከበቂ በላይ የሆነ መረጃ እንደ ጎሥጎሥ እልጠራጠርም። ለሥነ መለኮት ተማሪዎችና ተመራማሪዎች ትልቅ የመንደርደሪያ ሐብትም እንደሆነ እገነዘባለሁ።

ማዋሰድ አቅቶን እንጂ ለካንስ በታላላቆቻችን ሕይወት ታላላቅ መጻሕፍት ተሰውረው አሉ! እላለሁ።

(ወንድዬ ዓሊ)



# 1 መነሻዬ

## 1. ዘለቀ - የባሊ አቦዉ ልጅ

ቀኑን ርግጠኛ አይደለሁም፤ ሰኔ 2004 ዓ.ም፤ ቦታው ቀጠና ሁለት ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስትያን፣ አዲስ አበባ። ለየት ያለ ዝግጅት በቤተክርስትያኒቱ ተደግሷል። እጅግ ያማረና የደመቀ፣ የማይረሳ ዕለት። በርግጥ መንፈሳዊ ድግሱ የተዘጋጀው ለመጋቢዎች ብቻ ነበር። በተያዘው ፕሮግራም መሰረት የእኔ ተራ ሲደርስ ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ወደ መድረኩ አቀናሁ። አንድ ሁለት ርምጃ ተራምጄ ምስባኩ ላይ ተሰየምኩ። ማስታወሻ ደብተሬንና መጽሐፍ ቅዱሴን በምስባኩ ላይ በርጋታ አኖርኩና መነፅሬን አደረኩ። ከዚያም በተረጋጋ መንፈስ ቀና ብዬ ታዳሚውን ሁሉ ገረመምኩ። ከዳር እስከ ዳር ጢም ብሎ አዳራሹ ሞልቶአል። በቁጥር 4500 የሚሆኑ መጋቢዎች አይኖቻቸውን አቅንተው በማስተዋል እያዩኝ ነው። ሁሉም ላይ የተረጋጋ መንፈስ ይነበባል። ያረፈ ሕዝብ ። "ያዕቆብ ሆይ፥ ድንኳኖችህ (ማደሪያዎችህ) ምንኛ ያምራሉ!" የሚለው ቃል በልቤ ውስጥ አቃጨለ።

በእርግጥም እግዚአብሔር በልጁ ደም የዋጀው ሕዝብ እንዴት አያምርበት፣ እንዴትስ እይረጋጋ! የጉባኤው ፀጥታና ለተናጋሪው የሰጡት ፍፁም አትኩሮት ልናገር የቆምኩለት ጉዳይ ምን ያህል ቦታ እንደተሰጠው ያሳያል። በመንፈስ ቅዱስ

መሞላት በኢትዮጵያ እንዴት እንደተጀመረ እንደምናገር ቀደም ብሎ መነገሩ የሁሉም ጆሮ ስጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጥ ያደረገው ይመስለኛል::

ምስባኩ (መድረኩ) ላይ የተገኘሁበትን ጉዳይ በዝርዝር ከማንሳቴ በፊት ስለ ትውልድ መንደሬ፣ ስለ ልጅነት ሰፈሬ አንዳንድ ነገር ማለት ፈለግሁኝ:: እናም መጋቢዎቹን ጠየቅኋቸው:: ምናልባት የትውልድ መንደሬን፣ ባሊ አቦን ያውቋት እንደሆን:: ከዚያ ሁሉ መጋቢ አገልጋዮች ውስጥ ግን ባሊ አቦን የማውቀው እኔ ብቻ ነበርኩ:: ምናልባት ስለ መንደሯ ሰምተው እንደ ሆነም ለማወቅ ፈለጌ ከ4500 መጋቢዎች ውስጥ አንድ ባገኝ ብዬ ማተርኩ፤ እጅ ያነሳ ሰው ግን አልነበረም:: በዚህን ጊዜ በአንድ ስብሰባ ላይ መጋቢ ቶሎሳ ጉዲና የወንድም ዘለቀ የትውልድ ሰፈር በዓለም ካርታ ላይ እንኳ እንደማትገኝ ለተሰብሳቢው በማሳቅ የተናገረው ቃል ትዝ አለኝ::

የተወለድኩት በእድአ ወረዳ ባሊ አቦ በምትባል መንደር ነው::ቦታው በአካባቢው ሰዎች ካልሆነ በስተቀር ያን ያህል የሚታወቅ አይደለም:: በእርግጥም ሊያሳውቀው የሚችል ምንም ነገር የለውም:: አካባቢው ከብዙ የልማት እውታሮች ርቆ ከመገኘቱም በላይ የመጠጥ ውሀ ለመቅዳት እንኳ ከ30 ደቂቃ በላይ ወደ ሞጆ ወንዝ በእግር መጓዝን ይጠይቃል:: የእህል ወፍጮም በአካባቢው ስላልነበረ በባህላዊ የጉልበት ወፍጮ ቤት ውስጥ ካልተፈጨ በስተቀር እህል ለማስፈጨትም ቢሆን እስከ ደብረ ዘይት ድረስ መጓዝ ግድ ነበር:: ምንም እንኳ አካባቢው ታዋቂ ባይሆንም እኔ ግን የተወለድኩበትና ልጅነቴንም ያጣጣምኩበት ቦታ ስለ ነበር ለኔ ልዩ ትርጉም ነበረው፤ በተለይም ልጅ በነበርኩበት ጊዜ::

ወላጆቼ እንደ ነገሩኝ እናቴ የወለደችኝ በፅኑ ምጥ ነዉ፤ ሂደቱም ብዙ ጣጣ የበዛበት ነበር:: የኔም የእናቴ ሕይወትም የተረፈው በልምድ አዋላጇ ያላሰለሰ ጥረትና በፈጣሪ ተዓምር እንደ ነበር ከእናቴ ሰምቻለሁ::ገና በልጅነቴ ብዙ በሽታ የሚያጠቃኝ ነበርኩ:: በተለይ አንድ ጊዜ ከፉኛ ስለ ታመምኩ ወላጆቼም





እንደምሞት ርግጠኛ ነበሩ:: ኋላ ላይ ነፍስ ዘርቼ ስድን የእናቴ አባት አቶ ደስታ የተባሉ የተጉለት ሰው "በዚህ ህመም ካልሞተ በርግጥ ከአሁን በኋላ ምንም አይሆንም፤ በእግዚአብሔር ኃይል እስከ መጨረሻው በሕይወት ይዘልቃል!" ብለው ስሜን ዘለቀ ብለው እንደሰየሙ ይነገራል::

በእድሜ እያደግሁ ስሄድ የታዋቂውንና የተወዳጁን ቄስ የነበረውን የአባቴን ፈለግ ለመከተል ከነበረኝ ጉጉት የተነሳ ምንም ልጅ ብሆን አንኳ ብዙ ጊዜ እዘውትሬ ወደ ቤተክርስትያን እሄድ ነበር:: አባቴ ባልታወቀ ምክንያት በድንገት ወደ ናዝሬት (አዳማ) ከተማ ለመሄድ ልቡ ይነሳሳል:: ጊዜ አልፈጀም:: ወደ ናዝሬት አቀና:: በናዝሬት ማዘጋጃ ቤት የጸሐፊነት ሥራ አግኝቶ ጥቂት እንደቆየ ከዚያ ከምወደው መንደር፤ እትብቴ ከተቀበረበት ሰፈር ወደ ናዝሬት ወሰደን:: ናዝሬት ስንሄድ እኔ የሰባት ዓመት ልጅ ነበርኩ::

አባቴ ቀን ላይ መደበኛ የፀሐፊነት ሥራውን ሲከውን ይውላል:: ጠዋት ማታ ግን ከጸሎቱና ዳዊት ከመድገሙ ታክቶ አያውቅም:: የወላጆቼ ቤተክርስትያን አዘውታሪነትና የጸሎት ትጋታቸው በተለይም በልባቸው ያደረው ፈሪሐ-እግዚአብሔር ከፍ ያለ መንፈሳዊ ዝንባሌ እንዲኖረኝ ታላቅ ተፅዕኖ ነበረው::

ለእኔ የእግዚአብሔር መኖር አጠያያቂ አልነበረም፤ መንግስተ ሰማይና ገሐነም እሳት መኖሩም:: ምድርም የኑሮዬ ፍጻሜ እንዳልሆነችና በአጠቃላይ ከሞት ባሻገር ሕይወት መኖሩንም ተምሬአለሁ:: እኔም እንደ ወላጆቼ ቤተክርስትያን አዘውትር ስለ ነበር ስለ ገሃነመ እሳት/ሲዖልና ስለ መንግስተ ሰማይ በሰፊው ስምቻለሁ:: ሲዖል በጣም ያስፈራኝ ነበር:: ልገልፀው ከምችለው በላይ:: ርግጥ ነው ሲዖል ያስፈራል:: እኔ ወደዚያ ስፍራ በፍጹም መሄድ አልፈልግም:: በፍፁም !ግን እንዴት አመልጣለሁ? ወደ መንግስተ ሰማይስ እንዴት እገባለሁ? የዘወትር ጥያቄዬ ነበር:: በልጅነት አእምሮዬ የሚመላለስ የዘወትር ጥያቄ:: ከዚህም የተነሳ አባቴን በጥያቄ አጣድፈው ነበር:: "አባዬ!" "አቤት" "እንዴት

ነው ሰው ወደ መንግስተ ሰማይ የሚገባው? እኔስ እንዴት ወደ መንግስተ ሰማይ መግባት እችላለሁ? ሲያልንስ እንዴት ይሆን የማመልጠው?" "ደጋግ ሥራ ሥራ ፤ ሰድሀ መፅውት፤ ስትሞትም በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ ትገባሰህ!" የአባቴም የማያወላዳ የዘወትር መልስ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በምላሹ ውስጤ ረከቶ አያውቅም፡፡ እጠይቃለሁ፤ ይመልስልኛል፡፡የውስጥ ጥያቄዬ ግን አይመለስም፤ ነፍሴም የአባቴን መልስ አትቀበልም፤ መንፈሴም አይረካም፡፡ መጠየቄን ሳላቆም፣ ጥያቄዬም ሳይመለስ፣ ወደ መንግሥተ-ሰማይ መግቢያና ከሲያል ማምለጫ ቁልፉን ሳላገኝ፣ የደህንነት ዋስትና ሳይኖረኝ ወደ ወጣትነት/ጉርምስና ዕድሜ ደረስኩ፡፡

ምንም እንኳ የቤተክርስትያን እዘውታሪና የቄስ ልጅ ብሆንም ውስጤ በእግዚአብሔር መንገድ ላይ በእግባቡ የተተከለ ስላልነበርና ከብዙ ጥያቄዎችና ግራ መጋባቶች ጋር አብሬ ያደግሁ መሆኔ በወጣትነት ዕድሜዬ በአካባቢዬ ከሚኖሩት ልጆች ሁሉ በላይ በዱርዬነት የታወቅሁ ሆንሁ፡፡ በጊዜው በዋናነት የተጠላሁ ዱርዬ ያሰኙኝ ሶስት ነገሮች ነበሩ፡፡ እንደኛ (ናዝሬት ሲኒማ ቤት ስላልነበረ) ከቤተሰቦቹ እየተደበቀ ወንጂ ድረስ በመሄድ ከየት እንዳመጣው በማይታወቅ ገንዘብ ሲኒማ ይገባል፤ ሁለተኛ ሲጋራ ሲያጨስ ብዙ ጊዜ ይታያል፤ ሶስተኛ በየሳምንቱ ዐርብ ከትምሕርት ቤት ወደ ቤት እንደ ሄደ ፓስቲ (ጮርናቄ) ይበላል" የሚሉት ነበሩ፡፡ በርግጥ ሲኒማና ሲጋራ በጣም እወድ ነበር፡፡ በድሮ ሲኒማ ቤቶች ደግሞ ብዙ ጊዜ ሁለቱም አይነጣጠሉም ነበር፡፡ በነዚህ ምክንያቶች በሰፈሩ ባሉ በወላጆች ሁሉ ፊት በጣም የተጠላሁ ሆንሁ፡፡ ሆኖም ግን ያ በልጅነት ልቤ ውስጥ የፀለለው የመንግስተ ሰማይ ነገር ፈጽሞ አልተሰየኝም ነበር፡፡

ትዝ ይለኛል፤ በአንድ ወቅት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስቅለት የሚተርክ የድሮ ፊልም ናዝሬት በተከፈተው ሲኒማ ቤት ይታይ ነበር፡፡ እኔም አንድ ቀን ፊልም ለማየት ጎራ ባልኩበት ጌታን ሲገርፉትና ሲያንገላቱት፣ በመስቀልም ላይ ሲሰቃይ ሳይ በፍፁም ልቆጣጠረው የማልችለው ሃዘንና ለቅሶ ከውስጤ እየፈነቀለ ይወጣ





ነበር፡፡ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ፡፡ ሃዘኑ በቀላሉ ከውስጤ የሚወጣ አልነበረም ። ግን ለምን? ከዚያ በፊት ብዙ አሳዛኝ ፊልሞችን አይቼ አውቃለሁ፤ የሲኒማ አፍቃሪነቴና ደምበኝነቴም በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነው፡፡ እንደዚያ ቀን ግን ልብን የሚሰብር፣ ነፍስን የሚነካ ሃዘን አዝኜ፣ አልቃሻም ሆኜ አላውቅም፡፡ ያን ቀን ግን ሳግ እየተናነቀኝ፣ እምባ እየከዳኝ ብዙ አለቀስኩኝ፡፡በርግጥ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ግን አልገባኝም ነበር፡፡

ወደ ስምንተኛ ክፍል ስገባ ሚኒስትሪ ለማለፍ በጣም ተግቼ ለማጥናት ወሰንኩኝ፡፡ ከምሄድበትም ከብልሹ መንገድ ራሴን ለመቆጠብም ሞከርኩ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲያግዘኝ በማውቀው መንገድ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ጀመርኩኝ፡፡

የጸሎት ርዕሶቼ የትምህርቴና የባህርዬ ጉዳይ ሆኖ ሳለ በጸሎቴ መሃል "ስምንተኛ ክፍል ካለፍኩ አገለግልሃለሁ!" እል ነበር፡፡ ነገሩ ከአፌ ሲወጣ እኔም እሰማው ነበር እንጂ ምን ማለት እንደሆነ፣ ምን እያልኩ እንደሆነ እንኳ አይገባኝም ነበር ። "ማገልገል ማለት ምን ማለት ነው? ቄስ ሆኜ ነው ወይንስ ናዝሬት እንዳሉት የሚኖናይት ሚስዮናዊያኖች? ምንም አልረዳውም ነበር፡፡

አንድ ጊዜ ትዝ ይለኛል የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ ከትምህርት ቤት ወደ ቤቴ እየሄድኩ ልክ ቤቴ አጠገብ ስደርስ አንድ የማላውቀው ነገር ውስጤን በኃይለኛ ለላም ተቆጣጠረው፤ ባለሁበት ቆምኩኝ፡፡ በዛው ባለሁበት ቦታ ስቅስቅ ብዬ እያለቀስኩ "ጌታ ሆይ ለእኛ ለችግረኞች አንተ ባትኖርልን ምን ይውጠን?" እል ጀመር፡፡ ጥቂት ቆይቼ መለስ አልኩኝ፡፡ አሁንም ነገሩ አልገባኝም፡፡ ብጠይቅም መልስ አላገኘም፡፡ ከዚያም እንባዬን ጠራርጌ ወደ ቤት ገባሁ፡፡

ስምንተኛ ክፍል የተማርኩበት ዓመት ከሞላ ጎደል የሰላም ዓመት ሆኖልኝ ነበር፡፡ በባህሪዬም ሆነ በትምሕርት ጥናት በኩል ጥሩ ነበርኩ፡፡ በመጨረሻም የስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተፈትኜ እጅግ ጥሩ ውጤት አምጥቼ አለፍኩ፡፡ ሆኖም ግን ያንን ተስፋ የገባሁትን እግዚአብሔርን 'አገልግላለሁ!' ያልኩትን ፈጽሜ ረሳሁ፡፡ ቃሌን አጠፍኩበት፡፡ ድል አደረኩና የድሴ ደጀን የነበረውን አምላክ ችላ

አልኩት ።

ወደ ዘጠነኛ ክፍል ስገባ በኃጢአት ብዛት ወደ ታች እያሽቆለቆልኩ ሄድኩኝ፡፡ መሻሻል የጀመረው ባህርዬ መዝቀጡን ተያያዘው፡፡ በድል ማግስት ድር አደራብኝ፤ የከፋት ድር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ "ለኃጢአተኛ ሰላም የለውም" እንደሚል ሰላም ፈጽሞ ከእኔ ራቀ፡፡ የሚያስደስተኝ አንዳችም ነገር አጣሁ፡፡ ሕይወት ትርጉም አልባ ሆነችብኝ፡፡ የሚወዱኝ ጓደኞች ቢኖሩም ፍቅራቸው ውስጤ አይገባም ። ሰላም አጣሁ፡፡የምበላው፣የምጠጣው፣ የማየው የማደርገው ክቶ አያረካኝም ። ለመኖሬ ትርጉም አጣሁለት፡፡ ከዚህም የተነሳ 'ሰው ህይወቱን ቢያጠፋ የሚያስደንቅ አይደለም!' ያልኩባቸው ጊዜያት ጥቂቶች አይደሉም፡፡ እኔም ራሴን ያላጠፋሁት መንግስተ ሰማይ የመግባቴ ነገር ስላጠራጠረኝና የሲዖል እሳትም የማስፈራት ሃይሉ ስላስደነገጠኝ ይመስለኛል፡፡ ሰው ጊዜያዊ የሆነውን የምድር ሥቃዩን ካልቻለ ዘላለማዊ የሆነውን፣ ዕፎይታ የሌለበትን የዘለዓለም መከራና ፍዳ እንዴት ይችለዋል?

ባጠቃላይ ዘጠነኛ ክፍል ያሳለፍኩበት ዓመት በጣም አስፈሪና አስደንጋጭ ዓመት ሆነብኝ፡፡ በዚህም ምክንያት የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት ሴሚስተር የትምሕርት ውጤቶቼ ሁሉ በጣም ዝቅተኛ ነበሩ፡፡ ሆኖም በእግዚአብሔር እርዳታ የሁለተኛው ሴሚስተር ውጤቴ በጣም ስለተሻሻለ ወደ ሐረር መምሕራን ማሠልጠኛ ለመሄድ ተመረጥኩ፡፡

## 2. ሐረር መምሕራን ማሠልጠኛ

ጊዜው 1955 ዓ.ም፣ መስከረም ሲጠባ፣ እግሬ ሐረር ገባ፡፡ ሐረር እጅግ አረንጓዴ ከመሆኗም በላይ እጅግ ብዙ ፍራፍሬ የሚገኝባት ከተማ ነች፡፡ እስኪደንቀኝ ድረስ





ሌሎች አካባቢዎች ላይ ያላየኋቸው እንደ ጊሽጣና ወሽመላ ዓይነት ፍራፍሬዎች የፍራፍሬ ፍላጎቴን ጥግ አደረሱልኝ፡፡ ወቅቱ ደግሞ የዓመቱ መጀመሪያ እንደመሆኑ ሁሉም ነገር ልዩ ስሜት ይፈጥራል፡፡ እፅዋት በክረምቱ ዝናብ ፈክተው በመስከረም ሶሎራ ፀዳላቸውን የሚረጩበት፣ አእዋፋት ባማረ ዜማቸው ቅኔ የሚቀምሩበት፣ ነፋሻማ አየሩ፣ የሃገሩና የትምሕርት ቤቱም አዲስነት ያሉበትን አሮጌ ነገር ሁሉ ያስረሳል፤ መንፈስን ያድሳል፤ ተስፋን ያለመልማል፡፡

ኦ ሐረር! ሐረር በአቀማመጧም ሆነ በልምላሜዋ፣ በአየር ጠባይዋም ጭምር ትቼ ከመጣኋት ናዝሬት በጣም የተለየች ነበረች፡፡ የናዝሬትን አቧራ የሰለቸው ማንነቴ በሐረር ልምላሜ ተካሰ፡፡በሐረር የነበረው ሁኔታ ወደ ሐረር እንደገባሁ አንድ ዓይነት ለውጥ በሕይወቴ እንደሚመጣ ተስፋ አሳደረብኝ፡፡ መኖር መኖር አለኝ፡ ፡በርግጥ በውስጤ የነበረው አለመረጋጋትና ጥያቄ እንዳለ ቢሆንም የሐረር ሁኔታ ግን ስሜትን የሚጫን፣ተስፋን የሚጭር ነበር፡፡

ሐረር የመምሕራን ማሠልጠኛ ተቋም በሃገራችን ከነበሩት ቀደምት የእውቀት ልህቀት ማዕከሎች አንዱ ሲሆን በዚያን ጊዜ የሶስት ዓመት የመምህርነት ኮርስ የሚሰጥበት ትልቅ የመንግሥት የትምሕርት ተቋም ነበር፡፡ የተሰራበት ድንጋይና አጠቃላይ ገፅታው እጅግ ባማረና በቀላሉ ዐይን ውስጥ በሚገባ መልኩ ነበር፡፡ ከዚያ ተቋም የሚወጡ መምሕራን በሃገሪቱ ውስጥ መንግሥት በሚመድባቸው ስፍራዎች ሁሉ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን የማስተማር ሃላፊነት ነበረባቸው፡፡

ባጠቃላይ ሐረር ከተፈጥሮ ልምላሜዋ፣ ከማህበረሰቡ መልካምነትና ከታሪካዊ አቀማመጡዋ ጭምር ውጫዊ ርካታዎችን ሳትሰስት ሰጥታኛለች፡፡ ለልግስናዋ ወደር አልነበረውም፡፡ ሆኖም መንፈሳዊ የሆኑት ጥያቄዎቼ ግን መልስ አላገኙም ነበር፡፡ ነፍሴ ወጥራ ይዛኛለች፤ ልቤ ሙሉ ለሙሉ አልረጋም ብሎኛል፤ መንፈሴ ለመረዳት የማልችለው ዓይነት ቃተታ ይቃትታል፡፡ መልስ ግን የለም፡፡ ሚስጢሩ ግን አልተገለጠም፡፡ ሐረር ባላት ሁሉ መመለስ አትችልም፡፡ የተፈጥሮም ሆነ ሰው

ለራሽ ውበቶች አዚያ ጋ አይደርሱም፡፡ የሰው ልብ ጥልቅ ነው፤ ፈጣሪው ካልሆነ ፍጡር አያውቀውም፡፡

ትምሕርት ተጀመረ፡፡ ሁሉም ተማሪ በተመደበበት ከፍል ተገኝቷል፡፡ አብዛኞቹ ከየከፍለ ሐገሩ የመጡ ወጣቶች ነበሩ፡፡ እኔም በተመደብኩበት ከፍል ተገኝቼ አንድ አፍታ ተማሪዎቹን ሁሉ ገረመምኳቸው፡፡ አንድም የማውቀው ሰው አልነበረም፡፡ ብቸኛ መሆኔ ታወቀኝ፡፡ ነገር ግን ምንም አልመሰለኝም፡፡ ምክንያቱም ብቸኝነት ያደኩበትና ከራሴም ጋር ጊዜ እንዳሳልፍ፣ የነፍሴን ጥያቄና ርሃብ በውል ለመረዳትና ለመመለስም ጥረት የማደርግበት ስለሆነ አወደዋለሁ፡፡ ይህ በሐሪዬ አስከ ዛሬም አብሮኝ አለ፡፡

ሆኖም ግን በወጣትነት ዕድሜ ሁልጊዜ ብቸኛ ሆኖ ስለማይዘለቅ አንዳንድ ጓደኞችን ማፍራት ጀመርኩ፡፡እንግዲህ ሰው የሚያፈራው ቢጤውን ነውና በዚህን ጊዜ ካፈራኋቸው ጓደኞቼ አንዱ ጣሰው ዘለቀ ይባላል፡፡ ጣሰው አግር ኳስና ሲጋራ ነፍሱ ነው፡፡ ይሄ እኔንና ጣሰውን ያመሳስለናል፡፡ አብረን አናጨሳለን፤ ለትምሕርት ቤቱም ኳስ እንጫወታለን፡፡ በተለይ ቅዳሜ ቅዳሜ ከተማ ወርደን ሻይ መጠጣት፣ ባቅላባ መብላትና ሲጋራ ማጤስ ለእኛ ትልቅ መዝናኛዎቻችን ነበሩ፡፡

በጊዜ ሂደትም አንድ አዲስ ጓደኛ ጨመርን፤ ዓሰሙ ምናሴ ይባላል፡፡ዓለሙን ከኛ ጋር ያጣመረው ኳስ ተጫዋችነቱ ነበር፡፡ እንደኛ ግን ሲጋራ የማያጤስና ራሱንም በስነ-ምግባር የሚጠብቅ ወጣት ነበረ፡፡ ሶስታችንም የትምሕርት ቤቱ (ሐ ቡድን) ተጫዋቾች መሆናችን ለሦስታችንም ዝናና ከብርን አጎናፀፎናል፡፡በአጨዋወት ስልታችን፣ የኳስ ቅብብላችንና ጎል አገባባችን በትምሕርት ቤቱ ለተንሰራፋው አውቅናና ተወዳጅነት ያበቃን ሲሆን ስሞቻችንም የተያያዙ መሆናቸው በቀላሉ አንድንታወቅ አድርጎናል፡፡ ጣሰው ዘሰቀ፣ ዘለቀ ዓለሙ፣ ዓሰሙ ምናሴ፡፡

ሐረር፣ የሐረር መምሕራን ተቋም፣ ጓደኞቼ፣ ዝናና ከብር የውስጤን ጩኸት ለጊዜው ከማዳፈንና የአፍታ ደስታ በስሜቴ ላይ ከመጫር ባሰፈ አሁንም ድረስ ጥያቄን መመሰስ፣ ውስጤን ማረጋጋት፣ ሰላምን መስጠት ግን አልቻሉም፡፡





ሁሉም ነገር ከውጭ ያልፋል፤ ውስጤ ግን አሁንም ይጮሃል፡፡ ጩኸቱ ደግሞ ከኔ በስተቀር ለማንም አይሰማም፡፡

በመማሪያ ከፍላችን ውስጥ ከሁለቱ ጓደኞቼ በተጨማሪ አንድ እኛ ከምንቀመጥበት ወንበር ቀጥሎ ባለ ወንበር ላይ የሚቀመጥ፣ ደስ የሚልና የሚስብ ባሕርይ ያለው ሌላ ጓደኛ አገኘሁ፡፡ በማላውቀው ምክንያት ከእርሱ ጋር ተቀራረብን፡፡ እርሱ ከሌሎች ጓደኞቼ በጣም ለየት ያለ ነበር፡፡ ፈተና ሲደርስ አብረን እናጠናለን፡፡ ፍራፍሬ እንደኔ ይወድ ነበርና አብረን ፍራፍሬ እንበላለን፡፡ ሲጋራ እያጭስ እንጂ በመጠጥ በኩል እንቀራረብ ነበር፡፡ በርግጥ አንዳንድ ነገሮች ከእኛ ጋር ቢያደርግም ለየት ያለ ሰው እንደ ነበረ ይታወቀኝ ነበር፡፡

ወጣቱ ጌታቸው ምከረ ይባላል፡፡ አሁን እንደተረዳሁት ብዙም ጠልቆ አይግባው እንጂ ስለ ጌታ አየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ያውቅ ነበረ፡፡ የመጣውም ከአዲስ አበባ መርካቶ አካባቢ ስለ ነበረ አልፎ አልፎ ፊኒሽ ሚሽን ይሄድ እንደ ነበር ነልጾልኛል ። አንዳንድ ጊዜ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ነገር ይነግረኝ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ብዙም ጠልቆ በውስጤ የሚገባ ነገር አልነበረም፡፡

አንድ ቀን ለብዙ ወራት በውስጤ ሲቀር የቻለ ነገር ተናገረ፡፡ አዚያ አሱ ይከታተል በነበረው ፊኒሽ ሚሽን የቤተ ክርስቲያን መጋቢ የነበሩት ሴት ሚስዮናዊ ዛሬም እንደ ሐዋርያት ዘመን መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ ሲናገሩ ሰምቻለሁ አለኝ፡፡ ያህን ጊዜ ሃሳቤ ሁሉ ወደ ተናገረው ነገር ተሳበ፡፡ ምክንያቱን ግን አላወቅሁም፡፡ በውል ባይገባኝም ቃሉ ለመንፈሳዊ ጥያቄና ውስጤ ለተሰማው ነገር ሁሉ ርካታን ወደማገኝበት አውነት እንደ ተቃረብኩ ተሰማኝ፡፡ ስለ ነገሩ ለማወቅ ጓጓሁ፡፡ ውስጤ ላለፉት ዓመታት ለምንም ነገር እንደዚያ ጉጉት አድሮበት አያውቅም ። ለምን ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር ቀልቤ እንደ ተወሰደ አላውቅም፡፡ በተለይም 'በአሁኑ ዘመን ልክ እንደ ሐዋርያት ዘመን መንፈስ ቅዱስ ይሰጣል!' ሲል ነገሩ ፈጽሞ ገብቶኝ አይደለም፡፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሰማሁት ቄሱ አባቴ አልፎ አልፎ 'አገሌ መንፈስ ቅዱስ የቀረበው ሰው ነው!' ሲል ነበር፡፡ የሰውየውን ደግነትና ጥሩ

ሰው መሆኑን ለመግለጽ፡፡ ከዚያ በተረፈ ግን በዚህ ዘመን መስጠቱን ለመጀመሪያ ጊዜ መስማቴ ነው፡፡ ከመቀመጫዬ ቀና አልኩ፤ አንገቴን ወደሱ አሰገግሁ፤ ዐይን ዐይኑን እያየሁ ፈጠን ያለ ጥያቄ ጠየቅሁት፡ "እውነት ነው? እንደ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ አሉ ነው ምትለኝ? ከተቀበሉ በኋላስ ምን ይመስላሉ? ምን ዓይነት ለውጥ አሳቸው?" የጌታቸው መልስ አዎንታ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም እሱ የሰማውን እንጂ ያየውን አልነበረም ያጫወተኝ፡፡

"እኔ የማውቀው በዛ ሚሽን ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ኢትዮጵያዊ የለም ። የሚሰብኩት ሚስዮናዊያ ግን ተሞልተዋል" አለኝ፡፡ ይህን የነገረኝ በ1955 ዓ.ም ነበር፡፡ ከጌትሽ ጋር በጣም ተቀራረብን፤ ጓደኝነታችንም በጣም ጠነከረ፡፡ ጌትሽ እጅግ ትጉህና ትሁት ሰው ቢሆንም አንዳንዴ ኃይለኛነት ይታይበት ነበር፡፡ አንድ ጊዜ በክፍል ውስጥ ከጂኦግራፊ አስተማሪው ጋር ተጣልቶ (አንዲት ሰባራ ሴንቲ ነበረችው) "በዚህ ወግቼው አዲስ አበባ እገባለሁ!" አለ፡፡ "አዲስ አበባም ብትገባ የመሸፈቻ ቦታ አይደለም፤ ልትያዝና ልትታሰር ትችላለህ" ብለን በግድ ከሌሎች ተማሪዎች ጋራ ሆነን አባብለን ነበር ያስተውነው፡፡ ከዚህ በተረፈ ጠባዩ እንከን የሚወጣለት አልነበረም፡፡

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ አሳልፈን የ1955 ዓ ም የትምሕርት ጊዜ አገባደን፣ በሰኔ ወር መጨረሻ ትምሕርት ቤቱ ለክረምት ወራት ተዘግቶ ወደ የመጣንበት አካባቢ ተመለስን፡፡ ለእኔ ግን የመንፈስ ቅዱስ ነገር ከውስጤ የማይወጣ ነገር ሆነ፡ ፡ ወደ ናዝሬት ከተመለስኩ በኋላ እልፎ እልፎ እየተደበቅሁ ኃይለማርያም ማሞ ሆስፒታል በሚገኘው ሜኖናይት ሚሽን እየሄድኩ እሁድ እሁድ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ጀመርኩ፡፡ ብዙም ባይገባኝም ግን ቃሉ ሲነገር፣ ዝማሬው ሲዘመር ሁሉ ደስ ደስ ይለኛል፡፡ እልፎ እልፎም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጠኝ እጸልይ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ክረምቱን አሳልፌ እንደገና በ1956 ዓ.ም ለትምሕርት በመስከረም ወደ ሐረር ተመለስኩ፡፡





# 3. "አይበቃህም?!"

1956 ዓ.ም ከአምናው በተቃረነ መልኩ መስከረምና ጥቅምት በጣም ከባድና የጨለማ ጊዜ፣ የመኖር ተስፋዬም የመነመነበት ዓመት ሆነብኝ፡፡ በብዛት ሲጋራ ከማጤስ ጋር ተያይዞ ይመስለኛል ጠዋት ጠዋት ስነሳ ልቤን በኃይል የሚፍቅና ጉሮሮዬንም የማቃጠል ስሜት ይሰማኝ ጀመር፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ አንድ ቀን ከጓደኞቼ ጋር እንደተለመደው ከተማ ወርደን ባቅላባ በሻይ ከበላን በኋላ ሲጋራ አቀጣጥዬ ላጤስ ስል የሚያስገርም ድምፅ ሰማሁ፡፡ የተቀሩት እጠገቤ ያሉት ጓደኞቼ የሰሙት አይመስለኝም፤ ለእኔ ግን በግልጽ ይሰማኛል፡፡ "አትመለስም?! አይበቃህም?!" የሚል ድምፅ፡፡ ተናጋሪውን ለማየት ዞር ዞር አልኩ፤ ከጓደኞቼ በስተቀር ማንም የለም፡፡ ማንም ይሁን ማን ውስጤ ግን ደንግጧል፡፡ ወዲያውኑ ያቀጣጠልኩትን ሲጋራ አጥፍቼ፣ እዛው ጥዬ ጓደኞቼን "እኔ ወደ ትምሕርት ቤት አመለሳለሁ፡፡" ብዬ ጥያቸው ብቻዬን ፈጠን ፈጠን እያልኩ በመራመድ ወደ ትምሕርት ቤት ተመለስኩ፡፡ ወዴት ነው እምመለሰው ብዬም አልጠየኩም፤ ጥያቄዬም አልነበረም፡፡ ድምፁን በምሰማበት ወቅት ወዴት እንደምመለስ ልቤ ተረድቶ ነበር፡፡ ያን የጣልኩትን ሲጋራ ይኸው ከሃምሳ ዓመታት በላይ ተለየሁት፤ ሱሴም ያን ቀን ከላዬ ተራገፈ፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላ ተፈትኜበት እንኳ አላውቅም፡፡

በዚያን ጊዜ ከናዝሬት የመጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚ (Bible Academy) የመጡ ወጣቶች ዐርብ ዐርብ ማታ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይሰባሰቡ ነበር፡፡ ጌታቸው ምክረም እዚያ ይሳተፍ ነበር፡፡ ከአንዴም ሁለቴ የጋበዘኝ ቢሆንም ለመሄድ ፈቃደኛ አልነበርኩም፡፡ ምክንያቱም ሳያቸው በብዙ ሥራቸው ከእኔ የተለዩ ለሰሆኑ እነሱ መካከል መግባቴ ለእነርሱም ይሁን ለእኔ ተስማሚ አይሆንም ብዬ ስላሰብኩ ነበር፡፡ ከሲጋራ ማጨስ ሱስ ልላቀቅ እንጂ የውስጥ ዕረፍት፣ እርካታና ሰላም አልነበረኝም፡፡

## 4. ገደብ በሌለው ጸጋ መወረስ

ዐርብ ማታ፣ ህዳር 5 ቀን 1956 ዓ.ም ጌትሽን "ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁ ውሰደኝ" አልኩትና ወሰደኝ፡፡ ወጣቶቹ በደስታ ተቀበሉኝ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ ተጀመረ፡፡ የሚነጋገሩት ምንም ሊገባኝ አልቻለም፡፡ በውስጤም 'እኔ እንደ እነርሱ በዚህ በወጣትነት ዕድሜዬ መሆን አልችልም፤ ምናልባት 30 ዓመት ሲሆነኝ እንደ እነርሱ እሆናለሁ' ብዬ ጥያቸው ወጣሁ፡፡ ሃሳቤም የሚቀጥለው ሳምንት ፈተና ስለ ነበረኝ ከፍል ሄጄ ማጥናት ነበር፡፡ ግን ሳላውቀው ከትምህርት ቤታችን ቅጥር ግቢ ወደ ውጭ በምታስወጣው ስላች መንገድ ወጥቼ መሄድ ስጀምር ድንገት በተመስጦ ውስጥ ሆኜ በዕዝነ ልቡናዬ ጌታ እየሱስ ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ሲወድቅ ሲነሳ፣ በታላቅ ሲቃ ሆኖ ወደሚሰቀልበት ሲሄድ እመለከት ጀመርኩ፡፡ እንባዬን ልገታው አልቻልኩም፡፡ በጣም አለቅስ ነበር ። በርግጥ ከስተቱን በሥጋ አይኔ የማየውን ያህል ጥርት ብሎ ይታየኝ ነበር ። አይኔን ብጨፍን ብገልጸውም ያው በፊቴ ነበር፤ አልጠፋም፡፡

አሁን ጊዜው በጣም እየጨለመ መጣ፡፡ ከትምሕርት ቤቱም ቅጥር ጥቂት ራቅ ብሎ ያደጉ ብዙ የባህር ዛፍ ችግኞች ነበሩ፡፡ ከመንገዱ ወጣ አልኩና ወደ ችግኞች ውስጥ ገብቼ ተንበረከኩ (ለእኔ ይህ ነገር አዲስ ነው)፡፡ ከአፌ ውስጥ 'ጌታ ሆይ፣ እባከህ ለእኔ ለኃጢያተኛው እዘንልኝ!' የሚል ድምፅ ሲወጣ ሰማሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንብቤ አላውቅ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለም አላውቅም ብቻ ይህን እንዳልኩ ቦታው ወደ ኮረብታማነት ሲለወጥ እያለሁ፡፡

በዚያም ኮረብታ ላይ ባዶ መስቀል ተተክሎአል፡፡ ዐይኖቼን አንስቼ መስቀሉን እየሁ፡፡ ልክ መስቀሉን ሳይ ከላዬ ላይ፣ በተለይ ከትከሻዬ የሆነ ነገር ተነሳ ተነሳ፡፡ ከዚያም በውል በሚገባኝና በምረዳው መልኩ ሊገለፅ የማይችል ሰላም በውስጤ ተንቆረቆረ፡፡ እንደ ንፁህ ፈሳሽ ምንጭ በልቤ ፍስስ አለ፡፡ ከመንግስተ ሰማይ ጋር እንደታረቅሁ ታወቀኝ፡፡ ውስጤ ብቻ ሳይሆን አካባቢዬም በእግዚአብሐር ከብር ተሞላ፡፡ ወዲያው በውስጤ "ልጄ ሆይ በመንፈስ ቅዱስ እሞላሃለሁ፡፡" የሚል





ድምጽ ተሰማኝ፡፡ እኔ ግን ለዚህ ድምጽ ብዙም አትኩሮት አልሰጠሁትም፡፡ ከተንበረከኩበት እንደ ተነሳሁ ባገኘሁት ሰላምና ረፍት እጅጉን ተገረምኩ፤ እጅግም ደነቀኝ፡፡ 'ሰው በዚህ ምድር ሲኖር እንደዚህ ዓይነት ሰላምና ደስታ የውስጥ እረፍትና እፎይታ ሊያገኝ ይችላል ማለት ነው?' ብዬ ራሴን ጠየቅሁ፡፡ ከዚያም በአርካታና በርጋታ ከዛፎቹ ውስጥ ወጥቼ ወደ ትምሕርት ቤት ግቢ ተመልሼ ገባሁ፡፡ ስመለስ ግን ምድርን እየረገጥኩ ሳይሆን በአየር ላይ እየተንሳፈፍኩ ያመስለኝ ነበር፡፡

ልክ ወደ መኝታ ቤቴ ስደርስ ጌትሽና ጓደኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸውን ጨርሰው ሲወጣ አገኘሁትና "ጌትሽ ይህን እየሱስ የምትለውን ሳላገኝ አልቀረሁም" አልኩት፡፡ "በምን አወቅህ?" ብሎ ወዲያው ጠየቀኝ፡፡ "ምክንያቱም ገደብ የሌለው ሰላምና ደስታ በውስጤ ይንቆረቆራል" ስለው መልሶ "ልክ ነህ እርሱ በሰው ልብ ውስጥ ሲገባ እንደዚህ ነው የሚያደርገው አሉ" ብሎ መለሰልኝ፡፡ እኔም "ጌትሽ እየሱስ እኮ 'በመንፈስ ቅዱስ እሞላሃለሁ' ብሎኛል፡፡ ስለዚህም" (ከመኝታ ቤታችን በስተጀርባ የእግር ኳስ ሜዳ ነበር) "እዚያ ሄጄ እጸልያለሁ" አልኩት፡፡

ጊዜው ቢመሽም ጨረቃዋ የሚያስገርም ብርሃኗን ሰጥታለች፡፡ ወደ እግር ኳስ ሜዳው በዝግታ እየተራመድኩ ደረስኩ፡፡ ጌትሽ በቅርብ ርቀት እንደተከተለኝ ግን አላስተዋልኩም፡፡ አንድ ቦታ ላይ እንደ ቅድሙ ተንበርክኬ ስጸልይ የእግዚአብሔር ኃይል በኃይል መጣና ወደ ኋላዬ ወደቅሁ፡፡ ልቆጣጠረው ከምችለው በላይ ነበር ። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ፍቅር እንደ ተቀደሰ እሳት ወደ ውስጤ መግባት ጀመረ፡፡ በእውነት ለመናገር መንግስተ ሰማይ የገባሁ እንጂ ምድር ላይ ያለሁ አልመሰለኝም፡፡ ጌትሽ ባየው ነገር በጣም ተገርሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አንዳንዶቹን ይዞ መጥቶ እንዲያዩኝ አድርጎ ነበር፡፡ ለብዙዎቹ በጣም እንግዳ ነገር ነበር የሆነባቸው፡፡ ለእኔ ግን ለዘመናት በውስጤ የነበረውን መንፈሳዊ ጥያቄዎቼን ሁሉ መለሰልኝ፡፡ በውስጤም የመዳኔን ዋስትና አገኘሁ፡፡ የጌታ የኢየሱስ የመስቀል ሥራው ብቻ ከአብ ጋር አስታርቆኝ፣ የኃጢያትንም ስርየት ሰጥቶኝ፣

በዘለአለም ብርሃን መንግሥት ውስጥ ለመኖር የሚያበቃኝ እርሱ ብቻ እንደሆነ ተረዳሁ፡፡ ሌሎች መንገዶች ሁሉ ፍጻሜያቸው የዘለአለም ድቅድቅ ጨለማ፣ የማይጠፋም የእሳትና የጥፋት ፍርድ ውስጥ የሚያስገቡ መሆናቸውም ታወቀኝ፡፡ የሚያስገርመው ነገር ይህ የዘለዓለም እምላክ ለሰው ልጆች ገደብ የሌለው ፍቅር እንዳለው፣ በልጁ በኩል ሰዎችን ሁሉ ለማዳንና ከእርሱ ጋር አብረው እንዲኖሩ ለማድረግ ፈጽሞ ፈቃዱ መሆኑን በዚያች ቅፅበት መረዳቴ ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ በፍቅር ኃይል ተሞልቼ፣ በዚያች ደማቅ በነበረች የጨረቃ ምሽት እጆቼን ወደ ላይ ዘርግቼ፣ እኔ በሌለኝ በግጥም መልክ ለሰማይ እምላክ በሚያስገርም ዜማ ምስጋና እምልኮ ማቅረብ ጀመርኩ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ እኔው ራሴ ራሴን ስዘምር እሰማው ነበር እንጂ ከእኔ አሳብ የወጣ እልነበረም ፡፡ በተፈጥሮ ካልተሰጡኝ ነገሮች አንዱ ለጆሮ የሚጣፍጥ የዝማሬ ድምፅ ነበር ፡፡ በዚያች ሰዓት ግን ከዚያ በኋላም ያልተደገመ የድምፅ ማማር ተሰጥቶኝ ለዚህ ላታደገኝ ጌታ ዘመርኩለት፡፡

በዚህ ሰዓት እነዛ ከጌትሽ ጋር የመጡት እብዛኛዎቹ ከርስቲያኖች ጥለውኝ ሄደዋል፤ ጌትሽ ብቻ ቀርቷል፡፡ እጠገቤ ሆኖ ስዘምር የሰማኝ እሱም መደነቅና መገረም ተሞልቶ "እኔ እንደዚህ ዓይነት ጣዕም ያለው ዜማ፣ ሲሰሙት የውስጥ ነገርን የሚቀሰቅሰ ዝማሬ እልሰማሁም" አለኝና "ስትዘምር ግጥሞቹን ታውቃቸዋለህ? ወይም አስታውሰህ ልትጽፋቸው ትችላለህ?" ብሎ ጠየቀኝ፡፡ እኔም ምንም እንደማላውቃቸው፣ እንዲሁ ከውስጤ ፈንቅለው የወጡ ቃላቶች እንደሆኑ ነገርኩት፡፡ እርሱም በመገረም "ይህ እጅግ የሚያስደንቅ ነገር ነው!" አለ፡፡ ይህ የሆነው ህዳር 5 ቀን፣ ዐርብ ማታ ምናልባት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ወይንም ሶስት ሰዓት ገደማ ነበር፡፡ ከዚያም ተነሰተን ወደ መኝታ ከፍሎቻችን ሄድን፡፡

በዚያች ብሩክ ምሽት በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ባሳለፍኩት የሕይወት ዘመኔ ተኝቼ የማላውቀውን ጥልቅ የሆነ የሰላም እንቅልፍ ተኛሁ፡፡ የት እንደ ወደቅሁ እንኳ ሳላውቅ አድሬ የማለዳ የወፎች ጣፋጭ ዝማሬ ቀሰቀሰኝ፡፡ አይኖቼን





ስገልጥ ነግቷል፡፡ ለሊቱ አልፏል፡፡ እንደ ቋጥኝ እላዬ ላይ ሰፍሮ የነበረው የትናንት ህይወቴም አብሮ እልፏል፡፡ የነፍሴ ጥያቄም ተመልሷል፡፡ እሰይ ሌሊቱ ነጋ፡፡ እሰይ ውስጤም ተረጋጋ፡፡ የማለዳዋ ፀሐይ በመኝታ ከፍሴ መስኮት ፈገግ እያለች ነራ አለች፡፡

> ፀዳል የተሞላው የፀሐይዋ ጮራ፣
>
> ባረፈ ሰውነቴ ብርሃን ሲያበራ፣
>
> 'ይሄ በምድር ነው?' አለች ተጠራጥራ፤
>
> ነፍሴ ገብቷት ግራ፡፡

በዕውነት መንግስተ ሰማይ ልሁን ወይንም ምድር አላወቅሁም፡፡ በጀርባዬ ተንጋልዬ ደስ የሚል ፈገግታ ፈገግ እልኩኝ፡፡ ውስጤ በፍሰሐ ተሞላ፡፡ ፈገግታዬን ሳቅ አሸነፈው፡፡ ከልብ የሆነ ሳቅ፡፡ ሳቄን ሳግ ተቀበለው፤ የደስታ እምባ ካይኖቼ ኮለል እያሉ በጉንጮቼ ተንከባለሉ፡፡ ልቤ በሃሴት ከነፈ፡፡ በመሰቀል ሞቱና ትንሣኤው እነኚህን ለዓመታት ስፈልግ፣ ስኳትን ያጣኋቸውን በረከቶች ሁሉ ለሰጠኝ፣ እንደዚህ ላረገኝ ጌታ ከውስጤ ፈንቅሎ 'ካልወጣሁ' የሚል ውዳሴ ምሲጋና አንደበቴን ሞላው፡፡ እዳሪ ትምሕርት ቤት ባይሆንና በመኝታ ከፍሉ ሌሎች ተማሪዎች ባይኖሩ ጮኬ ባመሰግነው ደስ ባለኝ ነበር፡፡

የዛሬ ጠዋት ልምምድ ባለፈው ምሽት ወደ እሳቤ የመጣውን ጥያቄ መልሶልኛል ፡፡ 'ይህ ያገኘሁት ሰላም ዘላቂ ነውን? ወይንስ ቀስ እያለ በኖ ይጠፋል?' የሚለው ጥያቄ ከዚህ በኋላ ጥያቄዬ እይሆንም፡፡ ይሁንና ያገኘሁትን የውስጥ እፎይታና ሰላም ላለማጣት ከነበረኝ ሰስት የተነሳ ጠላት ይህን ጥርጥር በየቀኑ ወደ ልቤ ያመጣብኝ ነበር፡፡ ውስጤም በፍርሃት ይሞላ ነበር፡፡ 'ካጣሁት ምን እሆናለሁ?' አላለሁ፤ ከአሁን በኋላ እኔ ወደ ድሮ ኑሮዬ ለመመለስ አልፈልግም፡፡ 'ካጣሁት እንዴት መልሼ አገኘዋለሁ?' የሚሉ የነበረኝን ጨቅላ እምነቴን የሚፈታተኑ ሃሳቦች ያስጨንቁኝ ነበሩ፡፡

ዕለቱ ቅዳሜ ስለነበረ በእዳሪ ትምሕርት ቤታችን ቁርስ የምንበላው ረፈድፈድ

አድርገን ነው፡፡ ስለዚህም መኝታ ክፍሌ የተወሰነ ጊዜ ቆየሁና ልብሴን ለባብሼ፣ ፊቴንም ተጣጥቤ፣ ከመኝታ ቤታችን ወጥቼ ወደ ምግብ አዳራሽ መሄድ ስጀምር ሌላ በጣም የሚያስደንቀኝ ነገር ሆነ፡፡እዚያ ያሉትን ተማሪዎች በሙሉ ሳያቸው በጣም ወደድኳቸው፡፡ ሁሉንም አቅፌ ብስማቸው በጣም ደስ ባለኝ ነበር ። ለእኔ ይህ አዲስ ነገር ነው፡፡ በተፈጥሮዬም የነበረኝ ነገር አልነበረም፡፡ በዚያ ሰዓት ግን ሁሉም የሚወደዱ ነበሩ፡፡ ምድር እንደዚያ ያለ ውበት እንዳላት አስተውዬ አላውቅም ነበር። የተፈጥሮ ውበቷ ሁሉ ቀልቤን ገዛው፤ መገረም ሞላብኝ፡፡ተፈጥሮን የማድነቅም ልምድ ከዚያ በፊት አልነበረኝም፤ ማስደሰቱንም አላውቅም፡፡ በዚያ ሰዓት ግን ዛፉ፣ ሳር ቅጠሉ፣ የወፎች ዝማሬ፣ የቅጠሎች ልምላሜና ውዝዋዜ ሁሉ ለውስጤ ልዩ ትርጉም ይሰጠው ጀመር፡፡ በእርግጥ የእግዚአብሔር ቃል 'ምድር በእግዚአብሔር ግርማ ተሞልታለች' የሚለው ለእኔ በዚያ ሰዓት እውን ነበር፡፡

ከጌትሽ ጋር ወደ ቁርስ አዳራሻችን ገባንና ቁርሳችንን በላን፡፡ ከዚያ ስንወጣ ቀጥሎ ማድረግ ስላለብኝ ነገር ጥቂት ተመካከርን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ አልነበረኝምና ከአንድ ትንሽ የስዊዲሽ ሚሽን ቤተክርስቲያን ገዛሁ፡፡ ዕለት ዕለት ማንበብና ማጥናቴንም ተያያዝኩት፡፡ የቃሉም መረዳት ወደ ልቤ ይፈስ ነበር፡፡

አንድ ቀን ጌትሽን "የዛሬ ዓመት 'መንፈስ ቅዱስ እንደ ሐዋርያት ዘመን ይሰጣል!' ያልከኝ ትዝ ይልሃል?" ብዬ ጠየቅሁት፡፡ እርሱ ግን ምንም ትዝ ሊለው አልቻለም፡ ፡ እኔ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ህይወቴን ለጌታ እየሱስ ክርስቶስ መስጠት ማለት ምን እንደሆነ እንኳ ሳይገባኝ ልዑል እግዚአብሔር እንደ ሐዋርያት ዘመን መንፈስ ቅዱስን እንዲሞላኝ በክረምት ረፍቴ ብዙ እንደለመንኩት ነገርኩት፡፡ እርሱም ከሶስት ወር በፊት እዛ መርካቶ የምትገኘው የፊኒሽ ሚሽን አንድ ከኬኒያ የመጣ ቻቻ ኦማሄ የተባለ ሰው ስለመንፈስ ቅዱስ በአሁኑ ዘመን መስጠት አስተምሮ ሲፀልይ አንዳንድ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ልክ እኔ እንደምናገረው በአዲስ ቋንቋ መናገራቸውን፣ እነዚያም ሰዎች ስማቸው ከበደ ወልደማርያም፣





ሙሉስ ወጉና ፋንታሁን እንደሚባሉ አወጋኝ፡፡ እነዚህን ሰዎች ገና ሳላውቃቸው በውስጤ በጣም ወደድኳቸው፡፡እንዴት እንደማገኛቸውና እንደማያቸውም ማውጣት ማውረድ ጀመርኩ፡፡ ሆኖም ከአንዳቸውም ጋር የመገናኘት ዕድል አላገኘሁም (ከከበደ ወልደማርያም ጋ ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር በኋላ፣ በ1957 ዓ.ም ለአገልግሎት ጋብዘነው በመጣበት አጋጣሚ ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ የተያየነው፡፡

በጊዜው ያልተረዳሁት፣ በሕይወቴ የሆነው ነገር ምን ነበር? በርግጥ የኃጢያት ኃይል የገዛኝ፣ በዲያቢሎስ ግዛት ውስጥ የምኖር፣ በኃጢያቴና በበደሌ የሞትኩ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳች ቃል ኪዳን ያልነበረኝ፣ ያለ ክርስቶስ ተስፋቢስ የሆንኩና በኃጢያቴም ምክንያት የእግዚአብሔርን ፍርድና ቁጣ በላዬ ላይ ጭኜ፣ እግሮቼ ወደ ዘለዓለም ድቅድቅ ጨለማና ጥፋት እየፈጠኑ የምሄድ ሰው ነበርኩ፡፡ አንዳንዴ "ያኔ ራስን የማጥፋት አሳብ ሲመጣብኝ ብፈጽመው ኖሮ ዛሬ የት ነበርኩ?" ብዬ ትናንትን አስብና ይሰቀጥጠኛል፡፡ ዳግመኛ የእግዚአብሔር ምህረትና ይቅርታ በማይደርስበት፣ በሚያስፈራውና ልወጣ በማልችለው ዘለዓለማዊ ሲዖልና ጨለማ ውስጥ፣ ሰው ከስቃዩ ላፍታ እንኳ የእፎይታ ፋታ በማያገኝበት ነበልባል ውስጥ ገብቼ ለዘለዓለም ስስቃይ መኖሬ ነበር፡፡

እግዚአብሔር ግን በእውነት በምህረቱ እጅግ ባለ ጸጋ የሆነ አምላክ ነው፡፡ ለሰው ልጆችም ገደብ የሌለው ታላቅ ፍቅር ስላለው፣ የሚወደውን አንድ ልጁን ልኮ፣ ልጁም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ፣ የእኔን ርኩሰትና ኃጢያት ወሰደልኝ፡፡ይህም ብቻ አይደለም፤ በኃጢአት ምክንያት በእኔ ላይ የነበረውን የእግዚአብሔርን ቁጣና ፍርድ በመስቀል ላይ ሙሉ በሙሉ ተቀብሎልኝ፣ በሞቱና በትንሳኤው፣ በመስቀልም ላይ በፈሰሰው የከበረ ደሙ፣ የኃጢያቴን ስርየት፣ የነፍሴንና የመንፈሴን መንጻትና መቀደስ አረጋገጠልኝ፡፡ ከእብም ጋር በማስታረቅ በዘለዓለም የብርሃን መንግሥት ውስጥ የማይጠፋ ርስትን አስገኘልኝ፡፡

በእርግጥ 'ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገለጠ' የሚለው ቃል የታመነ ነው:: ጌታ እየሱስ ክርስቶስ፣ ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር ወልድ፣ ኃጢያት የማያውቀው አምላክ፣ ስለ ሰው ልጆች፣ ስለ እኔ ኃጢያት ሲል ስተሰቃየው ስቃይ ገደብ የለውም:: በእኛ ፋንታ፣ እኛ ልንከፍለው የሚገባንን የዘለዓለም ፍርድና ቁጣ እርሱ ወሰደው፤ ስለዚህም በደግ ሥራችን ሳይሆን፣ እርሱ በመስቀል ላይ በፈጸመው የቤዛነት ሥራ ከእግዚአብሔር ዘንድ በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጠን:: እግዚአብሔር አብም ልክ ልጁን እየሱስ ክርስቶስን በሚወድበት ፍቅሩ እኔንም አፈቀረኝ፤ እንደ ውድ ልጁም ተቀበለኝ::

በርግጥ እኛ ክርስትያኖች ጌታ እየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታችንና አዳኛችን አድርገን የተቀበልንበት፣ ሁለንተናችንን ለእርሱ ብቻ ያስረከብንበት አጋጣሚና ልምምዳችን የተለያየ ሊሆን ይችላል:: አንዳንዶቻችን ስሜታችንን መቆጣጠር እቅቶን የደስታ ስቅሶ አልቅሰናል፤ አንዳንዶቻችን ልንቆጣጠረው ባልቻልነው ሳቅ ደስታችንን ገልፀናል:: አንዳንዶቻችን ደግሞ በጊዜው ምንም ከወትሮው የተለየ ነገር አልተሰማንም:: እንዲያውም ጌታን የተቀበልንበትም ቀን ትዝ የማይለን ሰዎችም እንጠፋም:: ቁም ነገሩ እዚህ ላይ ሳይሆን፣ በእርግጥ ኃጢያተኞች መሆናችንን አውቀን፣በሥራችንም መንግስተ ሰማይ መግባት እንደማንችል ተረድተን፣ ሌላ አማራጭ በሌለው በጌታችን በእየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሥራ ብቻ አምነን፣ ልባችንን ከፍተን እሱን እንደ ጌታችን አዳኛችን ተቀብለን፣ በእርሱ ማረፋችን ብቻ ነው የድህነት ሚስጥሩ::ጌታ እየሱስ ክርስቶስን ወደ ህይወታችን በምንጋብዝበት ጊዜ፣ ምንም እንኳ የትኛውም ዓይነት ከወትሮው የተለየ ስሜት ባይሰማን፣ እሱን ግን በዕምነት ከተቀበልን መንፈስ ቅዱስ የሚያስደንቅን የጸጋ ሥራ በውስጣችን ይሰራል፤ አዲስ ፍጥረትም ያደርገናል:: ክብር ለስሙ ይሁን !

እንግዲህ ጌታን ስቀበል በጊዜው ባልረዳውም በህይወቴ የሆነው ግን ይህ ነው::





መጽሐፍ ቅዱስ 'ማንም በክርስቶስ ቢሆን እርሱ አዲስ ፍጥረት ነው' እንደሚለው፣ በጌታ እየሱስ በማመኔ፣ የክርስቶስ ደም ካጠበኝ በኋላ እግዚአብሔር አዲስ መንፈስ ሰጠኝ (ሕዝ. 36፡25-28)፤ ይህም 'ዳግመኛ ልደት' የምንለው ነው:: መንፈሱንም በውስጤ አኖረ፤ የፍቅሩንም ሕግጋት በልቤ ጽላት ላይ ፃፈ:: እንግዲህ የሆነው ሁሉ የሆነው እንደዚህ ነበር::ይህ ነገር ከሆነ ይኸው ከ50 ዓመታት በላይ አለፈው:: መንፈሱም ከእኔ አልተወሰደም፤ ሰላሙም ከእኔ አልራቀም:: ይልቁን ለጌታ ያለኝ ፍቅር፣ ምስጋናና አምልኮ እጅግ የላቀና የበዛ ሆኖልኛል::

## 5. ያልተዘጋጀሁበት የጨለማ ኃይል ውጊያ

በዚህ አዲስ ባገኘሁት የሕይወት ልምምዴ በጌታ እየሱስ ክርስቶስ ደስ እያለኝ ስጓዝ፣ በቅርብ ያሉ ጓደኞቼና በሩቅም የሚያውቁኝ የትምሕርት ቤት ባልደረቦቼ መለወጤ በጣም ያስገርማቸው ጀመር:: እኔም ይህ ለውጥ ለቆኝ የማይሄድ፣ ከእኔ ጋር እስከ መጨረሻው እንደሚቆይ እያረጋገጥሁ መጣሁ:: የሚቀጥለው የክርስትና ጉዞዬም በመጽሐፍ ቅዱስና በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እንደዚሁም ከእኔ ባልተለየኝ ጌታቸው ምክረ ድጋፍ ቀጠለ:: እሁድ ዕሁድም በዛች እነስተኛ የስዊዲሽ ሚሽን እየሄድኩ የእግዚአብሔርን ቃል ስሰማ፣ ዝማሬያቸውንም አብሬ ስዘምር በጣም ያልጠበኩት ያልተዘጋጀሁበት ከባድና አስቸጋሪ መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ገባሁ:: ለካስ የማይታየን፣ የነፍሳችን ጠላት፣ የጌታ የእየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሥራ ተቃዋሚ የሆነ 'ዲያቢሎስ' የሚባል ጠላት አለ! ያ ከፉ የመጣበትና የተጠቀመባቸው ሰዎች በእየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት የማያምኑ ሰዎች ብቻ አልነበሩም፤ እንዲያውም በዱርዬነቴ የሚያውቁኝ፣ ኋላም ላይ ከብዙ መጥፎ ሱስ መላቀቄ፣ የረጋሁና ጭምት መሆኔ ያስደስታቸው ሰዎችም እንደ ነበሩ እሰማም፣ አስተውልም ነበር::

የደረሰብኝን ታላቅ የመንፈስ፣ የነፍስና የአእምሮ ውጊያና ጭንቀት ስናገር፣ በጥቂቱም ቢሆን የማውቃቸው፣ ዐርብ ዐርብ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የማገኛቸውን፣ እልፎ አልፎ ማታ ማታ ከአራት በኋላ ከመኝታ ቤታችን ጀርባ፣ በእግር ኳስ ሜዳ ላይ አብሬአቸው የምጸልየውን ወገኖቼን ለመውቀስ አይደለም፡፡ በእርግጥ በዚያን ጊዜ ያ የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ ምን ዓይነት ልምምድ እንደሆነ ማንኛችንም የጠሰቀ መረዳት አልነበረንም፡፡ የእግዚአብሔርን ቃልም እያወጣሁ በድፍረት ቃሉ እንደዚህ ይላል ለማለት እቅሙም ዕውቀቱም አልነበረኝም ። አጠቃላይ ትኩረቴም ሕይወቴ በጌታ ሠላም መሞላቱ፣ እፎይታና እረፍት ማግኘቴ፣ በእኔ ላይ የነበረው ማንኛውም ሰንሰለት መበጠሱ ላይ ብቻ ነበር፡፡

ወንድሞቼ ዐርብ ዐርብ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸው ስሄድ ከእኔ ጋር ሰመቀመጥ እሰመደሰታቸው፣ በጸሎትም ስፍራ ብዙም ሊቀርቡኝ እሰመውደዳቸው ይታወቀኝ ጀመር፡፡ በመጨረሻም የእኔ የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ፣ እንደውም ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከሰይጣን እንደሆነ መወራት ተጀመረ፡፡

እንድ እንግሊዛዊ ሚስዮናዊ ማን እንደ ጠራቸው ባላውቅም ከትምሕርት ቤታችን ፊት ሰፊት፣ ከቅጥሩ ውጭ እንዲት ትንሽ ድንኳን ተከለው የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምሩ ጀመር፡፡ በትምህርታቸው በጣም እባረክ ስለ ነበር ማታ ማታ ከራት በኋላ እየሄድን በዚያች ትንሽ ድንኳን አካባቢ ወደ አስርና እስራ ሁለት የምንሆን ተማሪዎች እናዳምጣቸው ነበር፡፡ አንድ ቀን ምሽት ላይ ተጠይቀው ይሁን በራሳቸው ተነሳሽነት ባይገባኝም፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማስተማር ጀመሩ፡ ፡ ትምህርታቸውም በአሁኑ ዘመን መንፈስ ቅዱስ እንደ ሐዋርያት ዘመን እንደማይሰጥ የሚያትት ነበር፡፡ በትምህርታቸውም ውስጥ ያ ሁሉ የቀድሞው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የመጨረሻው ሐዋሪያ ሲሞት ማቆሙን፣ 'በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተናል' እያሉ 'በልሳን እንናገራለን' የሚሉ ሰዎችም ውሸተኞችና





ልምምዳቸውንም ከአጋንንት እንደሆነ፣ እንዲያውም በቻይና አገር አንዲት ሾዮናዊት 'ልሳን ነው' ብላ ስትናገር ከአዳማጮች መካከል የምትናገረውን ልሳን የሚያውቅ ነበርና 'በልሳኗ እግዚአብሔርን ትሳደባለች' ብሎ እንዳጋለጣት ከአንድ በቻይና ከቆየ ሚሲዮናዊ ጓደኛቸው እንደሰሙ ተናገሩ፡፡

በዚህ ጊዜ ምን ልበላቸው፤ እንዴትስ የውስጤን ላስረዳ፤ ልቤ ተሰነጠቀብኝ፡፡ የሆንኩትና ያስተማሩት ትምሕርት ለየቅል ነበር፡፡ 'ሰካስ እኔ በምናገረው ልሳን ያንን፣ የምወደውን፣ የሞተልኝን ጌታ እየተሳደብኩ ነው' ብዬ ኃይለኛ ጭንቀት ውስጥ ገባሁ፤ የጠላትም ድምጽ በኃይል 'እዎ እየተሳደብክ ነው፡፡ ስለዚህ በዘለዓለም የፍርድ ቅጣት ትቀጣለህ፡፡ ይህ ሁሉ ልምምድህ ውሸት ነው፤ ዘለቄታም የለውም' እያለ አስፈሪና አስደንጋጭ በሆነ አሳብ የመንፈሴን መታወክና ጭንቀት አባባሰው፡፡

ስብሰባው እንዳለቀ ቅስሜ ተሰብሮ፣ ልቤ አዝኖ እየቆዘምኩ ወደ ዶርሜ ተመለስኩ ። ሌሊቱን እንዴት ልተኛ፤ ከፍሌ ሁሉ በጨለማ ኃይላት ተሞላ፤ የሚወረውሩት የቃላት ፍላጻ አዕምሮዬን እስከስት ድረስ የበረቱ ሆኑ፡፡ ከዚያ በኋላ ለብዙ ቀናት በዚያ ኃይለኛ ጭንቀትና ስቃይ ውስጥ አሰፍኩ፡፡ መብላትም ሆነ ትምህርቴን መከታተል፣ ማጥናትም ተሳነኝ፡፡ ለብቻዬ ወደ ጫካ እየሄድኩ መፀለይ ጀመርኩ፡፡

የሚገርመው ነገር ስጸልይ የእግዚአብሔር ኃይል ወደ እኔ ይመጣል፤ እልረዳውም ነበር እንጂ መንፈስ ቅዱስም በልቤ ውስጥ 'በልሳን ስትናገር ወደ ክብሬ መገኘት ያስገባህ የሰምን?' ይለኝ ነበር፡፡ ያንን በብዙ እቅጣጫ የሚናገረኝን የመንፈስ ቅዱስ ድምጽ ማስተዋል እቃተኝ፡፡ ከጊዜ በኋላ የእግዚአብሔርን ቃል ሳውቅ የገባኝ ነገር ቢኖር፣ መንፈስ ቅዱስ ሲናገረኝ የነበረው ሁሉ በቃሉ ውስጥ የተጻፈውን ነበር፡ ፡ ሆኖም ግን እኔ ሃሳቤን የሰጠሁት በአዕምሮዬ ሰሚወረወረው የሰይጣን የእሳብ ፍላጻ ብቻ እንጂ በውስጤ ሰሚናገረኝ፣ በጸጥታ በውስጤ ሰሚፈስው የመንፈስ ቅዱስ ድምጽ አልነበረም፡፡

በዚህኛው ልምምድ ለነፍሴ የማይተኛ ጠላት እንዳለ፣ እስኪገድለኝና እስኪያጠፋኝ ድረስ የማያርፍም እንደሆነ ተረዳሁ:: የክርስትና ህይወቴ የ'ሃሌሉያ' ብቻ ሳይሆን፣ በየፈርጁ ከዚህ ዓለም ገዢ ጋር ፍልሚያ የማካሂድበት ዓለምም እንደሆነ በዚያ በጨቅላ የዕምነት ጉዞዬ ተረዳሁ:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆ ከውኃው እንደ ወጣ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳያ ወርዶበት፤ ከዚያም በቀጥታ ከዲያቢሎስ ሊፈተን በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ወደ ምድረበዳ እንደ ሄደ ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው:: ይህም የሚያስተምረን በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላት በኋላ የሚቀጥለው ደረጃ ከጨለማ ሰራዊት ጋር ፍልሚያ እንደሚጠብቀን ነው:: በዚያ የሕይወት  መንገድ ቀደም ብለው የሄዱ ካሉልን ፈተናው በተወሰነ መጠን ቀለል ሊልልን፣ ቶሎ በድል እንድንወጣም እምነት ሊሆኑን ይችላሉ:: እነሱ የጠላትን በጌታ መስቀል ላይ መሸነፍ ሲነግሩን፣ እርሱ የሚናገረው ሁሉ ውሸት እንደ ሆነ ከህይወታቸው እየጠቀሱ ሲያወጉን እምነታችን ይጸናና ሳንዘገይ ፈተናውን በድል እንወጣለን:: የእግዚአብሔርም ቃል "እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ፣ ከምስክርነታቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት" ይላል እኮ (ራዕ. 12፡11):: ለእኔ ግን ይህ አልሆነልኝም:: ይህንን የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ በአካባቢያችን የተቀበለ ስላልነበረ ጌታ በጸጋው ብቻ የመጣብኝን እንድወጣው ያደረገ ይመስላል:: በእንደዚህ ያለ ወቅት የምናሳልፋቸው ማንኛውም የሕይወት ልምምዶች በኋላ ላይ የማይረሱ፣ ለሌሎችም የምናስተምራቸው፣ ጠቃሚ ትምህርቶችን ይሰጡናል፤ በርግጥ ለእኔ እነዚያ ዘመናት፣ ከዚያ በኋላ ለነበሩት የአገልግሎት አመታቶቼ ተዝቆ የማያልቅ ትምሕርት  አስጨብጠውኝ ነበር ያለፉት::

ውጊያው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ፣ እንዲያውም እኔ የማላውቀውን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለውን ፍርድ፣ ጠላት እያመጣ በብዙ ጭንቀት ይሞላኝ ጀመር:: ይባስ ብሎ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቴን እንድጠራጠር ከማድረግም አልፎ ተርፎ መዳኔንም ጥያቄ ውስጥ እንድከት አደረገኝ:: "በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ይቅርና መዳንህንስ በምን ታውቃለህ?  ያ ሁሉ ያሳለፍከው ልምምድ ሁሉ ውሸት ነው ። እንዲያውም አንተ የተመደብከው ለዘለዓለም ጥፋት ስለሆነ፣ እግዚአብሔርም ስለማያይህ፣ ዛሬም ሞትክ የዛሬ ዓመት ልዩነት እያመጣም፤ ምድብህ ከሚጠፉት ወገን ስለ ሆነ ለምን ዛሬውኑ ራስህን አታጠፋም?" የሚል ድምፅ ይሰማኝ ነበር:: እንግዲህ ነገሩን እጅግ በጣም የከፋ የሚያደርገው፣ የማልፍበትን የመከራ ሕይወት የምነግረው፣ የማዋየውና አብሬው የምጸልየው ሰው አለመኖሩ ነበር:: መቼም የወንድሞች የህብረት በረከት እንገብጋቢነት እጅግ ጎልቶ የሚታየን እንደዚህ ዓይነት ምድረ በዳዎች ሲከቡንስ አይደል (መዝ. 133፡1-3)! በእነዚያ ወራት ጌታ ምህረት ባያደርግልኝና ጸጋውንም ባያበዛልኝ ኖሮ፣ ራሴን ለመግደል ድፍረት ባይኖረኝም በእርግጥ አዕምሮዬን እጣ ነበር፤ ምናልባትም ደግሞ ከጥቅም ውጪ እሆን ነበር:: ሆኖም ግን ጌታ ለእኔ የተለየ ዓላማ ስለ ነበረው፣ ይኸው እስከ ዛሬ ኖሬ፣ ከ 50 ዓመታት በኋላ፣ በዚያው በሰጠኝ መንፈስ ቅዱስ ሃሴት እያደረግሁ፣ እያፈቀርኩትና እያገለገልኩት፣ በጤናማ አዕምሮ አለሁ::

ሰይጣን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላን አማኝ ሊፈትነውና እንደኔ ሊያስጨንቀው ከሚችልባቸው መንገዶች የእግዚአብሔርን ቃል በውል አለማወቅ የእንበሳውን ድርሻ ይይዛል (ሆሴ. 4፡6):: ለእኛ ለአማኞች ዲያቢሎስ አንድ ጊዜ፣ ለመጨረሻም ቢሆን የተሸነፈ ጠላት ነው:: ይህን እርግጠኛ ሆነን ማወቅ ይገባናል:: አለቆችና ስልጣናትን በመስቀል ላይ ድል ነስቶ፣ ትጥቃቸውን ካስፈታ በኋላ፣ ምርኮኞች መሆናቸውን በይፋ እያዞረ አሳያቸው (ቆላ. 2፡15):: ጌታ ዲያቢሎስን ድል የነሳልን ለእኛው ነው:: ስለዚህም ነው ዳግመኛ በተወለድን ቅፅበት፣ እግዚአብሔር አብ ከጨለማው መንግሥት  አውጥቶ፣ ወደ ፍቅር ልጁ ብርሃን መንግሥት ውስጥ ያፈለሰን::ይህ ማለት ደግሞ ሰይጣን በእኛ ላይ ሊሰለጥን ምንም ዓይነት ህጋዊ መብት የለውም ማለት ነው:: እስተውሉ የሰይጣን ኃይሉ በመስቀል ላይ ተወስዶበታል:: በእኛ ላይ የሚሰለጥነው እኛ በምንሰጠው ስልጣን እንጂ በዲያቢሎስነቱ  ኃይል ኖሮት አይደለም:: የተነጠቀ ስልጣኑን በማሳየትና በማሳሳት፣ ከእኛው በፈቃዳችን መልሶ እየወሰደ ነው:: ስለዚህ ማታለል የሰይጣን

ትልቁ መሳሪያው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ስለዚህም ነው የእግዚአብሔር ቃል 'ሕዝቤ ባለማወቁ ምክንያት ይጠፋል' ያለው፡፡

በክርስቶስ ማን እንደ ሆንን፣ ምንስ እንደ ተደረገልን አለማወቃችን ሌላኛው ትልቁ ክፍተታችን ነው፡፡ ጌታ እየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት፣ ለኃጢያት ስርየት ብቻ ሳይሆን፣ ያልተፈጠረውን፣ ጅማሬና ፍጻሜ የሌለውን፣ የራሱን የዘለዓለም ሕይወት ሊሰጠን ነው፡፡ይህ የዘለዓለም ሕይወት፣ የዘለዓለም እምላክ ግዛትና መንግሥት ውስጥ፣ በዚህ ዓለም እንድንኖር የሚያስችለን ነው፡፡ በክርስቶስ ትንሳኤ ያገኘነው ሕይወት፣ ከሁሉ የላቀና በማንም ከቶ የማይሸነፍ ሕይወት ነው፡፡ የመሬት ስበት ህግ እንዳለ ሁሉ፣ ትንሳኤም በእኛ ውስጥ እንደ ሕግ የሚሰራ ነው፡፡ ቃሉ እንደሚለው 'በክርስቶስ እየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም፤ ምክኒያቱም በክርስቶስ እየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአት ሕግና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶናል' (ሮሜ 8፡1-2)፡፡ የኃጢአት እና የሞት ሕጎች በዲያቢሎስ ግዛት ውስጥ የሚሰሰጥኑ ሕጎች ናቸው፡፡ እኛን ግን ጌታ እየሱስ በእርሱ ባለው፣ የሕይወት መንፈስ ሕግ፣ ማስትም በትንሳኤው ኃይል ነጻ አውጥቶናል፡፡ስለዚህ ሞትና ጨለማ የዲያቢሎስ ግዛት እንደሆነ ሁሉ፣ በክርስቶስ ያገኘነውም ሕይወት የእግዚአብሔር መንግሥት ግዛት ነው፡፡ስለዚህም በዚህ መንግሥት ግዛት ውስጥ ስለምንኖር፣ ዲያቢሎስና ጭፍሮቹ በእኛ ላይ ሊሰስጥኑብን ከቶ አይቻላቸውም፡ ፡ጌታም የመጣበት ዋና አላማ በዚህ ሕይወት ሊያኖረን ነው፡፡ ጌታ እየሱስ ራሱ 'እኔ የመጣሁት ሕይወት እንዲሆንላችሁ፣ እንዲበዛላችሁም ነው' ባለው መሰረት፣ አንድ አማኝ ማወቅ ያለበት፣ በዚህ እጅግ ኃይለኛ በሆነ በዘለዓለም ሕይወት ውስጥ መኖሩን፣ ይህም ሕይወት ከእግዚአብሔር አብ ጋር ያስተሳሰረው ሕይወት መሆኑንና የጠላትም ኃይል የማይሰስጥንበት መሆኑን ነው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ፣ በደሙ ውስጥ ያለውን ታላቅ ስልጣን ማወቃችን፣ ከጨለማ ስልጣናት ጋር በሚኖረን ውጊያ፣ በርግጠኝነት አሸናፊነትን እንድንቀዳጅ ያደርገናል፡፡ በመስቀል ላይ የፈሰሰው ደሙ የኃጢያት ስርየትን፣ መንጻትንና





ከአብ ጋር መታረቅን ብቻ ሳይሆን ፈጽሞ መቀደስንም ሰጥቶናል፡፡ የክርስቶስ ደም የውስጥ ሰውነታችንን ፈጽሞ የመቀደስ ኃይል አለው፡፡ ይኸውም ጠላት አቅም ስማሳጣት የሚወረወረውን የከስና የኩነኔ ቃል፣ በቀደሰን በደሙ ኃይል ስለምናሸንፈው፣ በውስጡ ሰውነታችን ለመጋጠምና ለማሸነፍ አቅምና ብርታት ይኖረናል፡፡ ሰድል አድራጊነት ኑሮ እነዚህ እውነቶች በጣም አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ቃሉም እንደሚናገር በቃላቸው ምስክርነትና በበጉ ደም ድል ነሱት ይላል፡፡ ክብር ለእርሱ ይሁን፡፡

በአራተኛ ደረጃ፣ በጌታ እየሱስ ስም ውስጥ ገደብ የሌለው የእግዚአብሔር ኃይል ስላለ፣ የዚህን ስም ኃያልነትና አሸናፊነት በውል ልንረዳው ይገባናል፡፡ በእርግጥ ስሙ የሚሰራቸው በጣም አስደናቂና አስገራሚ ሥራዎች አሉ፡፡የእግዚአብሔር ቃል 'ስሙን እየሱስ ትሰዋለህ፤ ህዝቡንም ከኃጢያታቸው ያድናቸዋል፡፡ ...በስሜ አጋንንትን ታስወጣላችሁ ...አብ በስሜ የምትጠይቁትን ሁሉ ያደርግላችኋል' ይላል (ማቴ፣ 1፡21፣ ማር. 16፡17 ዮሐ. 16፡23)፡፡ሆኖም ግን ከዚህም ጋር አብሮ በጣም የሚያስደንቀው፣ ጌታ እየሱስ ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው በተገኘው፣ በስሙ ውስጥ ያለው ስልጣን ነው፡፡"እግዚአብሔርም ያስ ልከ ከፍ ከፍ አደረገው፤ ከስሞች ሁሉ የሚበልጠውን ስም ሰጠው፤ በዚህም ስም በሰማይ ያለው፣ በምድር ያሉ፣ ከምድርም በታች ያሉ ሁሉ ይንበረከካሉ (ፊል. 2፡9-11)፡፡ በምድር ያለነው አማኞች በዚህ ስም መዳንን ስላገኘን ለዚህ ስም እንንበረከካለን፡፡አሁን ግን በምድር ላይ ያሉት እብዛኞቹ የሰው ልጆች፣ ይህን ስም ሲያከብሩት አይታዩም፡፡ ነገርግን ጊዜ ይመጣል፤ የሰው ልጆች ሁሉ ሳይወዱ በግድ 'እየሱስ ጌታ ነው' እያሉ ለዚህ ስም የሚንበረከኩት፡፡ ነገር ግን ያ ጊዜ ለመዳን የሚሆንላቸው አይደለም፤ የስሙን ኃያልነት በማወቅ ሳይወዱ የሚንበረከኩሰት ጊዜ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ቃል 'ከምድር በታች ያሉ ሁሉ ለዚህ ስም ይንበረከካሉ' ይላል፡ ፡ እነዚህ 'ከምድር በታች ያሉ' የተባሉት የጨለማ ስልጣናትና ኃይላት ናቸው፡፡ እየሱስ የሚለው ኃያል ስም በተጠራ ቁጥር፣ የሚኖሩበት የሞትና የጨለማ ግዛት

ከመሰረቱ ይናወጣል። ስለዚህም ሳይወዱ፣ በዚህ ስም ውስጥ ያለው ኃይል፣ አስገድዶ ያንበረክካቸዋል።

እንግዲህ እንደ አማኝ ማወቅ ያለበት፣ በዚህ ስም ውስጥ ያለው ኃይል በሙሉ፣ በዚህች ምድር ሲኖር፣ የጨለማ ኃይላትን ለማሸነፍ በስጦታ መልክ እንደተሰጠው ነው። እነዚህ እውነቶች ከገቡን የጨለማ ስልጣናት በእኛ መስልጠናቸው ቀርቶ፣ እኛ እንሰስጥንባቸዋለን። እኔ ግን በዚያ በጨቅላ የዕምነት ጅማሬዬ ላይ እነዚህ እውነቶች ስላልተገለጡልኝ፣ ጠላትም ደግሞ አለማወቄን በመጠቀሙ፣ በብዙ መከራ ውስጥ እንዳልፍ ሆንኩኝ። እግዚአብሔርም ያንን የፈቀደበት ምክንያት አለው።

ወደዚህ የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ ውስጥ ስንገባ፣ በተለይም ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቃችንና በልሳንም መናገራችን፣ የጨለማ ግዛቱን የሚያፈርስበት፣ የረቀቀ ሥራውንም በጸጋ ስጦታዎች የሚገልጥበትና በግዛቱ ውስጥ ያሉትን ብዙዎችን ከእጁ እየፈለቀቀ የሚያወጣበት እንደ ሆነ ሰይጣን ስለሚያውቅ፣ ቢቻለው ከመጀመሪያው በእንጭጩ ለመቅጨትና ለማጥፋት የማይፈነቅለው ድንጋይ፣ የማይበጥሰው ቅጠል እንደሌለ እንድረዳና ኋላም ላይ እንዳጋልጠው ይመስለኛል በእነዚያ ወራት በመንፈሳዊ ዓለማት ውስጥ የሚካሄዱትን ነገሮች እንድረዳ ጌታ ያስቻለኝ። እናም ጠላት ያሰበው ሳይሆን፣ ጌታ ግን ለእኔ ያቀደው ተፈጸመልኝ፤ ባፈቀረኝ በእርሱ፣ ቀስ እያልኩም ቢሆን ከፈተናዎቼ ውስጥ መውጣት ጀመርኩ፡ ፡ የመንፈስ ቅዱስም ኃይልና ብርታት በሙላት ተመለሰልኝ። መጽሐፍ ቅዱሴንም ሳነብ የቃሉ መረዳት ይመጣልኝ ጀመር። ሆኖም ግን በልሳን ስናገር፣ ያ ጠላት አዕምሮዬን የመረዘበት ኃሳብ እየመጣ፣ ለጥቂት ወራትም ቢሆን ማስቸገሩ አልቀረም ነበር።ይሁንና እንዳንዴ ሳላስበው እራሴን በልሳን ስናገር እገኘው ነበር። ጌታ ሁልጊዜ የጠላት ኃይል እይሎብኝ እንድንኖር እንደማያደርግና የጠላቴ ኃይሉ ሁሉ የሚገታበት፣ እኔም በደስታና በሀሴት እንድኖር ጌታ የሚያደርግበት ዘመን እንዳለ ገባኝ። ለጠላቴም የሚገባበትን ቀዳዳ ክቶ አለመክፈት በጣም አስፈላጊ





እንደሆነም ተረዳሁ።

ከዚዜ በኋላ አዕምሮዬ ሁሉ ከውጊያ አረፈ። ያ ዐርብ ዐርብ የምንሰበሰብበት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ግን ቆሟል። ቢሆንም ግን ፀሎቱ ቀጥሏል። በሳምንት ሁለት- ሶስት ምሽት ከእራት በኋላ፣ ከዶርማችን (ከመኝታ ቤታችን) ጀርባ በሚደረገው የ25 ደቂቃ ጸሎት እዘውትሬ መሳተፍ ጀመርኩኝ። የፀሎቱ ሁኔታ ባያረካኝም ከእነርሱ ጋር ህብረቴን ለመቀጠል ስል መካፈል ነበረብኝ። በግሌም ለረጅም ሰዓታት የምጸልይበት ስፍራም ነበረኝ። የፆም ጸሎት አስፈላጊነትም ጉዳይ ወደ ልቤ ይመጣ ጀመር። ቁርስና ምሳዬን እየተውኩ ራት ብቻ እየበላሁ መጸለይ ጀመርኩኝ። ይህም ለመንፈሳዊ እድገቴ እንድ እመርታ ሰጠኝ።

በጣም የሚያስገርመው ነገር፣ በዚህ በ1956 ዓ.ም የትምሕርት ዓመት፣ በብዙ ሁኔታ ውስጥ ባልፍም፣ እንድም እኔ የማውቀው፣ ወደ ጌታ የመጣ ሰው ግን አልነበረም። ጌታቸው፣ እርሱ በሚያውቀው፣ የእኔ ልምምድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን እኔን ደግፎ ይናገር ነበር። በዚህ ሁኔታ የትምሕርት ወራቱም እሰቀና ሰኔ 30 ትምሕርት ቤቱ ሲዘጋ እኔ ወላጆቼ ዘንድ ወደ ናዝሬት የክረምቱን ወራት ለማሳለፍ ሄድኩ።

ናዝሬት በክረምት ወራት በጣም ደስ የምትል ከተማ ነች፤ በዝናቡ ምክንያት አቧራው ያቆማል፤ ፀሐይም ያን ያህል የምታቃጥል አትሆንም። በክረምቱ ወራት ብዙ የአዲስ እበባ ሰዎች ስለሚመጡባት በጣም ትደምቃለች። እኔ ግን ጊዜዬን የማሳልፈው በቤቴ ውስጥ ሲሆን፣ ሲመሻሽ ደግሞ በእቅራቢያዬ ወደነበረ ጋራ በመሄድ ለረጅም ሰዓታት በመንፈስ ቅዱስ በመጸለይ ነበር። በየእሁዱም ሜኖናይት ሚሽን እየሄድኩ የእግዚአብሔርን ቃል እሰማ ነበር። በተለይ እንድ ጊዜ 'ወጣት ለክርስቶስ' የሚባል ፕሮግራም ውስጥ ተገኝቼ፣ አንዲት ከሐረር የመጣች ኢትዮጵያዊት እህት Joys are flowing like a river when the

comforter has come (እጽናኙ ሲመጣ ደስታ እንደ ወንዝ ይፈሳል) የሚለውን መዝሙር ስትዘምር ልቤ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንባዬ ይፈስ ጀመር:: ቃላቱ ስለ ማረከኝ አጠናሁት፤ በዚሁ በማያምረው ድምጼ ያን መዝሙር መዝሙሬ አደረግሁት፤ ብዙ ጊዜም እዘምረው ነበር::

አንድ ቀን ምሽት ቤተሰቦቼን ሰብስቤ ይህን ያገኘሁትን ልምምድ ለመንገር ወሰኝ ተነሳሁ::እንዴት እንደሚመሰከር ግን አላውቅም ነበር:: ነገር ግን በዚያች ምሽት ሁሉንም ሰበሰብኳቸውና የሚከተለውን አልኳቸው:: "እኔና እናንተ ተለያይተናል፤ ምክኒያቱም ልክ እንደ ሐዋርያት እኔ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቼ፣ በአዲስ ቋንቋ ስለምናገር ስሞት መንግስተ-ሰማይ ነው የምገባው" አልኳቸው:: ትዝ ይለኛል፤ በአባቴ ፊት ላይ የነበረው ታላቅ ኅዘን:: በቃ በእርግጥ ያበድኩ መሰለው:: በመጨረሻም ጌታ ነፍሳቸውን እንዲያድን ፀለይኩላቸውና ስብሰባው ተቋጨ::በሕይወቴ ያለውን ታላቅ ለውጥ አይተዋል::ቀድሞ ከማውቃቸው በከተማ ውስጥ ካሉ ከድሮ ጓደኞቼ ጋር አልገጥምም፤ እዘውትሬ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበቤንና መጸለዬን ብቻ ነው የሚያውቁት:: ታዲያ አንድ ቀን ፀሐይዋ እሽቆልቁላ ወደ መግባት ስትቃረብ፣ ውጭ በረንዳው ላይ ቁጭ ብዬ ያንን የምወደውን የእንግሊዘኛ መዝሙር joys are flowing like a river when the comforter has come እያልኩ መዝሙሩን በሙሉ ስዘምር አጠገቤ ተቀምጣ የነበረችው ሁለተኛዋ እህቴ በኃይል ጮሃ፣ መኝታ ቤቱ ገብታ፣ እንዴት እንደተረዳቻው አላውቅም ብቻ ሕይወቷን ለጌታ ሰጥታ ዳነች:: ዛሬ በሙሉ ወንጌል ታላቅ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ነች:: እንግዲህ በእኔ ሕይወት ምክንያትነት ለመጀመሪያ ወደ ጌታ የመጣችው እበበች ዓለሙ ሆነች:: ከዚያም በጣም የሚያስገርም የሕይወት ለውጥ በእርሷም ላይ ይታይ ጀመር:: ጌታ እየሱስ ክርስቶስንም እጅግ የምትወድ፣ ለእርሱም የተሰጠች እህት ሆነች:: ከዚያም የክረምቱ ወራት አለቀና በመስከረም 1957 ዓ.ም ወደ ሐረር መምሕራን ማሠልጠኛ ተመለስኩ::



# 2 አስደናቂው ጰንጠቆስጠአያዊ እንቅስቃሴ አጀማመር

## 6. ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ 'ፍንዳታ'

በመስከረም 1957 ዓ.ም ወደ ሐረር እንደ ተመለስኩ ወዲያው ጌትሽን አገኘሁት:: ሰላምታ ከተሰጣጠን በኋላ ከረምቱ እንዴት እንደ ነበረ ጠየቀኝ::እኔም በተለይ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላቱና በመንፈስም ስለ መጸለዬ፣ ከዚህም የተነሳ እጅግ በጣም የሚያስገርም ከረምት እንዳሳለፍኩ እጫወትኩት:: ከድሮ ጓደኞቼም መሃል የተወሰኑቱ ሊጠይቁኝ ቤት ድረስ መጥተው ጥቂት ከተጨዋወትን በኋላ፣ የቀድሞው ዓይነት ግብዣ ሲያደርጉልኝ፣ እኔ የተለወጥኩ ሰው መሆኔንና በድሮ መንገዴ መሄድ እንደማልችል እንደ ነገርኳቸው፣ አንዳንዶቹ ግን "ከሐረር ተመርቀህ ስትወጣና የመጀመሪያ ደሞዝህን ስታገኝ፣ ይህ የያዝከው ሕይወት እንደሚያቆም እርግጠኞች ነን" እንዳሉኝ፣ እኔ ግን በመንፈሳዊ ህይወቴ በጌታ በጣም እየበረታሁ፣ የጌታም ፍቅር በብዛት እየገባኝ፣ በሙሉ ዕረፍትና ሰላም ከረምቱን እንዳሳለፍኩኝ ለጌትሽ አወጋሁት::

ነገሩ ብዙም ግልፅ ባይሆንልኝም አንዳንዴ ጌታን የማገልገል አሳብ በውስጤ እንደሚመጣ፣ እኔ ያገኘሁትን መዳን ለሌሎች ለማሳወቅ እንደምፈልግም ነገርኩት:: ጌትሽም "ከፊኒሽ ሚሽን ይዤልህ የመጣሁት ነገር አለኝ" ብሎ ከመኝታ